www.abyssinialaw.com


# ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ

## የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ
የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 15 ዓመት ቁ. 1
መቐለ ለካቲት 10/1999 ዓ/ም

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፀ

15ኛ ዓመት ቁ. 1
መቐለ የካቲት 10/1999 ዓ/ም


## ኣዋጅ ቁፅሪ 116/1999 ዓ.ም

## ተማሓይሹ ዝወፀ ሕጊ ቤተሰብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ

ቤተሰብ መሰረት ሕብረተሰብ ብምኳኑ ብሕብረተሰብን መንግስትን ሓለዋ ክግበረሉ ዝግባእ ምኳኑ ብምእማን ሓለዋ መንግስቲ ዝግለፀሉ ሓዲኡ መንገዲ ርክብ ቤተሰብ ብሕጊ ምድንጋግ ወይ ክውሰን ምግባር ኣድላዪ ምኳኑ ብምርዳእ፤

ኣብ ሃገርና እናተሰርሓሉ ዝነበረ ሕጊ ቤተሰብ ኢትዮጵያ ኣብ ቀንዲ መትከላቱን ትሕዝትኡን ምስ ሕገ-መንግስታዊ ስርዓትናን ምስ ዝበፅሕናዮ ደረጃ ዕብየትን ክጠዓዓም ብዘይምኽኣሉ፤

ኣብ ፆታ ኣፈላላይ /ዘይማዕርነት/ ርክብ ተመስሪቱ ፍትሒ ክንዳል ብምፅንሑ ኣብ ማዕርነታዊ ርክብ ዝተመስረተ ቤተሰብ ንምህናፅን ብኡ ኣቢሉ'ውን ፅኑዕ መሰረት ዘለዎ ሕብረተሰብ ንምህናፅ ዘየኽእል ብምንባሩ፤

## አዋጅ ቁጥር 116/1999 ዓ.ም

## ተሻሽሎ የወጣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ

ቤተሰብ የሕብረተሰብ መሰረት በመሆኑና በሕብረተሰብና በመንግስት ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን በማመን፤ የመንግስት ጥበቃ የሚገለጽበት አንዱ መንገድም የቤተሰብ ግንኙነትን በሕግ መደንገግ ወይም እንዲወሰን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በመረዳት፤

በአገራችን በስራ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ በዋና ዋና መርሆዎቹና ይዘቱ ከሕገ-መንግስታዊ ስርዓታችንና ከደረስንበት የእድገት ደረጃ ሊጣጣም ባለመቻሉ፤

በፆታ ልዩነት /እኩልነት ያልተመሰረተ/ ላይ ተመስርቶ ፍትሕ ሲጓደል በመቆየቱና በእኩልነት ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ቤተሰብ ለመፍጠርና በዚህም ፅኑ መሰረት ያለው ሕብረተሳብ ለመገንባት የማያስችል ሆኖ በመቆየቱ፤

www.abyssinialaw.com



ብሓፈሻ ካብዞም ልዕል ክብሉ ዝተገለፁ መሰረታዊ ፀገማት ብምብጋስ ምስ ዝበፃሕናዮ ደረጃ ምዕባለ ዝሰማማዕ ኮይኑ ተማይሹ ክምሓዱሽ ክመዓራረ ኣድላይ ምኳኑ ብምእማን ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ብኣዋጅ ቁፅሪ 33/91 ዓ.ም ሕጊ ምውፅኡ ብምዝካርና፣ ኮይኑ ግና በዚ ኣዋጅ ሕብረተሰብና ኣብ ቀረብኡ ፍትሒ ክረክብን ቀደም ዝነበሩ ፀገማት ኣብ ምፍታሕ ዓብይ እጃም ዘወፈየ እኳ እንተኾነ ሓደስቲ ጠቐምቲ ሓሳባት ምውሳኽ ኣድላይ ምኳኑ ብምእማን፣

ስለዝኾነ እቲ ኣብ ስራሕ ዘሎ ሕጊ ቤተሰብ ትግራይ ዝተማልአ ብዘይምኳኑ ኣብ ኣፈፃፅማ ፀገም ይፈጥር ዘሎ ምኳኑ ብምግንዛብ ንሕብረተሰብና ብዝግባእ ግልጋሎት ምሃብ ብዘኽእል ኣግባብ ምቕራፅ ኣድላይ ምኳኑ ብምእማን፣

ሕጊ ቤተሰብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ምስ ተመሳሰልቲ ሕጊ ቤተሰብ ካልኦት ክልላት ዝመሳሰለሉን ዝቀራረበሉን ኣግባባት ምፍጣር ንኣፈፃፅማ ምችውነት ዝፈጥር ምኳኑ ብምእማን፣

ቤት ምኽሪ ክልል ትግራይ ተማሓይሹ ብዝወፀ ሕገ መንግስቲ ትግራይ ዓንቀፅ 49/3/ሀ/ ብዝተውሃቦ ስልጣን መሰረት እዚ ዝተመሓየሸ ሕጊ ቤተሰብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ኣውጺኡ'ሎ።

1. ሓጺር ርእሲ

እዚ ኣዋጅ "ተመሓይሹ ዝወፀ ሕጊ ቤተሰብ ትግራይ ኣዋጅ ቁፅሪ 116/1999 ዓ/ም" ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

## ምዕራፍ ሓደ

## ብዛዕባ ዝምድናን ሓዳርን ብሓፈሻ

ዓንቀፅ 1. ስጋ ዝምድና

1. ብዝምድና ምትእስሳር ዝርከብ ካብ ስጋ ዝምድና እዩ፣
2. ኣብ መንጎ ወለድን ተወላድን ብቀጥታ መስመር ዝቑፀር ምትእስሳር ዝምድና እዩ፣



በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተገለጹት መሰረታዊ ችግሮች በመነሳት ከደረስንበት የእድገት ደረጃ የሚስማማ ሆኖ እንደ አዲስ እንዲሻሻልና እንዲስተካከል አስፈላጊ መሆኑ በማመን የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 33/91ዓ.ም ሕግ ማውጣቱ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሆኖም ግን አዋጁ ሕብረተሰባችን በአቅራቢያው ፍትሕ እንዲያገኝና ቀደም ብለው የነበረበትን ችግሮች በመፍታት ረገድ ድርሻውን ያበረከተ ቢሆንም አዳዲስ ጠቃሚ ሓሳቦች መጨመር ኣስፈላጊ መሆኑን በማመን፣

ስለሆነም በስራ ላይ ያለው የትግራይ የቤተሰብ ሕግ የተሟላ ባለመሆኑ በአፈጻጸም ላይ ችግር እየፈጠረ ያለ መሆኑን በመገንዘብ ለሕብረተሰባችን በሚገባ አገልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ መቅረጽ አስፈላጊ መሆኑን በማመን፣

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ ከሌሎች ተመሳሳይ ክልሎች የቤተሰብ ሕግ ጋር የሚመሳሰልበትንና የሚቀራረብበትን አግባቦች መፍጠር ለአፈጻጸም አመቺነት የሚፈጥር መሆኑን በማመን፣

የትግራይ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የትግራይ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49/3/ሀ/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የተሻሻለው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ ኣዋጅ "ተሻሽሎ የወጣው የትግራይ የቤተሰብ ህግ ኣዋጅ ቁጥር 116/1999 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ስለዝምድናና ስለጋብቻ በጠቅላላው

አንቀጽ 1. የስጋ ዝምድና

1. በዝምድና መተሳሰር የሚገኘው ከስጋ ዝምድና ነው፤
2. በወላጅና በተወላጅ መካከል በቀጥታ መስመር የሚቆጠር ያዝምድና መተሳሰር ነው፤

www.abyssinialaw.com



3. ካብ ሓደ ኣቦን ኣደን ዝተወለዱ ወይ ብሓደ ወላዲ ጥራሕ ብዝራኸቡ ሰባት ናብ ጎኒ ዝቖፀር መስመር ትውልዲ እዩ፡፡

## ዓንቀፅ 2. ብርኪ ስጋ ዝምድና

1. ኣቆፃፅራ ስጋ ዝምድና ሓበራዊ መበቆል ካብ ዝኾነ ወላዲ ዝርከብ ብርኪ ዝምድና የማንን ፀጋምን ካብ ዘለዎ መስመር ትውልዲ ጀሚሩ ክሳብ ሻውዓተ ትውልዲ እዩ፤
2. ስጋ ዝምድና ካብ ሻውዓይ ብርኪ እንተሓሊፉ ውፅኢት የብሉን፡፡

## ዓንቀፅ 3. ዝምድና ሓዳር

1. ሓዳር ዝምድና ካብ ሓዳር ይርከብ፤
2. ሰብኣይ ካብ ሰበይቱ ጀሚሩ ንላዕሊ ምስ ዝቖፀሩ ወለዲ ወይ ንታሕቲ ምስ ዝቖፀሩ ተወለድቲ፤ ሰበይቲ ካብ ሰብኣያ ጀሚሩ ንላዕሊ ምስ ዝቖፀሩ ወለዲ ወይ ንታሕቲ ምስ ዝቖፀሩ ተወለድቲ ቀጥታ ዝኾነ ዝምድና ሓዳር ኣለዎም፤
3. ሰብኣይ ምስ ናብ ጎኒ ዝቖፀሩ ኣዝማድ ሰበይቱ፤ ሰበይቲ ድማ ምስ ናብ ጎኒ ዝቖፀሩ ኣዝማድ ሰብኣያ ዝምድና ሓዳር ኣለዎም፡፡

## ዓንቀፅ 4. ዝምድና ሓዳር ብዝምልከት ብርኪ ብዛዕባ ምቑፃር

ዝምድና ሓዳር ናብ ጎኒ ካብ ዝቖፀሩ ሳልሳይ ብርኪ ዝምድና እንተሓሊፉ ውፅኢት የብሉን፡፡

## ዓንቀፅ 5. ብክልተ ወገን ዘሎ ዝምድና ሓዳር

1. ሰብኣይ ምስ ሰበይቲ ዘሙኡ ምስ ሰበይቲ ሓኖኡ ወይ ድማ ምስ ሰበይቲ ሓሙታ ወይ ምስ ሰብኣይ ንዕልታ ድርብ ዝኾነ ዝምድና ሓዳር ኣለዎም፤
2. እዚ ድርብ ዝኾነ ዝምድና ሓዳር ውፅኢቱ ልክዕ ከምቲ ተራ ዝኾነ ዝምድና ሓዳር እዩ፡፡

## ዓንቀፅ 6. ምቁራፅ ዝምድና ሓዳር

ምኽንያት ምትእስሳር ዝምድና ሓዳር ዝኾነ እንተፈረሰ'ኳ ብሓዳር ዝተረኽበ ቀጥታዊን ጎናዊን ምትእስሳር ዝምድና ሓዳር ዝፀንዐ ይኸውን፡፡



3. ከአንድ አባትና እናት የተወለዱ ወይም በአንድ ወላጅ ብቻ በሚገናኙ ሰዎች መካከል ወደ ጎን የሚቆጠር የትውልድ መስመር ነዉ፡፡

## አንቀጽ 2 የስጋ ዝምድና ደረጃ

1. የስጋ ዝምድና አቆጣጠር የጋር ከሆነ የአንድ ወላጅ የዝድምና ደረጃ ጀምሮ ግራና ቀኝ ካለው ትውልድ መስመር እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ነው፤
2. የስጋ ዝምድና ከሰባተኛ የትውልድ ደረጃ ካለፈ ውጤት የለውም፡፡

## አንቀጽ 3. የጋብቻ ዝምድና

1. የጋብቻ ዝምድና ከጋብቻ ይገኛል፤
2. ባል ከሚስቱ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች ጋር፤ ሚስት ከባልዋ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች ጋር ቀጥታ የሆነ የጋብቻ ዝምድና አላቸው፤
3. ባል ከሚስቱ የጎን ዘመዶች፤ ሚስት ደግሞ ከባሏ የጎን ዘመዶች ጋር ወደ ጎን የሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና አላቸው፡፡

## አንቀጽ 4. የጋብቻ ዝምድና በሶስተኛ ደረጃ ስለመወሰኑ

የጋብቻ ዝምድና ወደ ጎን ከሚቆጠር ሶስተኛ የዝምድና ደረጃ ካለፈ ውጤት የለውም ፡፡

## አንቀጽ 5. በሁለቱ በኩል ያለ የጋብቻ ዝምድና

1. ባል ከሚስቱ ወንድም ሚስት ፤ ወይም ከሚስቱ እህት ባል፤ ሚስት ከባልዋ ወንድም ሚስት ወይም ከባልዋ እህት ባል ጋር ድርብ የሆነ የጋብቻ ዝምድና አላቸው፡፡
2. የዚህ ድርብ የሆነ የጋብቻ ዝምድና ውጤቱ ተራ ከሆነው የጋብቻ ዝምድና ነው፡፡

## አንቀጽ 6. የጋብቻ ዝምድና መቋረጥ

ዝምድናውን ያስገኘው ጋብቻ ቢፈርስም በጋብቻ የተገኘው የቀጥታና የጎን ዝምድና መተሳሰር እንደጸና ይኖራል፡፡

www.abyssinialaw.com



## ዓንቀፅ 7. ዝምድና ውላድ ጡብ (1) መትከዪ

ውዕል ሓደ ውላድ ጡብ ስጋ ዝምድናን ሓዳር ዝምድናን ብመሰረት ድንጋጊ ምዕራፍ ዓሰርተ ሓደ እዚ ሕጊ ክቐውም ይኽእል፡፡

## ዓንቀፅ 8.(2) ውፅኢት

ኣብ ዓንቀፅ 9 እዚ ሕጊ ዝተደንገገ ከምዘለዎ ኮይኑ ውላድ ጡብ ብዝኾነ መልክዑ ከም ውሉድ እቲ ብውላድ ጡብ ዘዕበ ዘሎ ሰብ ኮይኑ ይቑፀር፡፡

## ዓንቀፅ 9(3) ዝተሓበዉ ኩነታት

1. ውላድ ጡብ ንዝገብሮ ሰብ ንላዕሊ ዝቐፀሩ ወለዲ ወይ ንጎኒ ዝቐፀር ዝምድና ዘለዎም ነቲ ውላድ ጡብ ዝቓመሙዎ ምኻኖም እንድሕር ኣፋሊጦም ርክብ እቲ ውላድ ጡብ ኣብ ልዕሊኦም ምንም ዓይነት ውፅኢት ኣየስዕብን፡
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝቐርብ ተቓውሞ ውዕል ውላድ ጡብ ካብ ዝፀደቐሉ ዕለት ጀሚሩ ክሳብ ሓደ ዓመት ኣብ ውዕል መዝጋቢ ኣካል ቀሪቡ እንተዘይተመዝጊቡ ፈራሲ እዩ፡፡
3. ውላድ ጡብ ኣብ ልዕሊ'ቶም ውላድ ጡብ ዝገበሩ ሰብኣይን ሰበይቲን ከምኡ'ውን ኣብ ልዕሊ ደቆምን ዝፀንዐ ይኸውን፡፡

## ዓንቀፅ 10. ተፈጥራዊ ቤተሰብ ውላድ ጡብ

1. ውላድ ጡብ ምስ ተፈጥራዊ ቤተሰቡ ዘለዎ ዝምድና ምትእስሳር ከምዘለዎ ይነብር ፣
2. ከምኡ'ውን ውላድ ጡብ ኣብ ልዕሊ ዝኾነ ሰብ÷ ሰብኣይ ወይ ሰበይትን ተወለድትን ምትእስሳር ዝምድና ይፀንዕ፡፡

## ምዕራፍ ክልተ

## ኣፈፃፅማ ሓዳር

## ዓንቀፅ 11. ዝተፈላለየ ኣፈፃፅማ ስርዓታት ሓዳር

1. መርዓ ኣብ ቅድሚ ሓዳር ከምዝግብ ዝቖመ መንግስታዊ ኣካል ክግበር ይኽእል፣
2. ከምኡ'ውን ብሃይማኖት ወይ ሃገር ልማድ ክልቲኦም ተመራዕውቲ ወገናት ዝግበር መርዓ ብሕጊ ተቐባልነት ኣለዎ፡፡



## አንቀጽ 7. የጉዲፈቻ ዝምድና (1) መሰረቱ

በአንድ የጉዲፈቻ ውል የስጋ ዝምድናና የጋብቻ ዝምድና በዚህ ሕግ ምዕራፍ አስራ አንድ መሰረት ሊቋቋም ይችላል፡፡

## አንቀጽ 8 (2) ውጤት

በዚህ ህግ በአንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም አስተያየት የጉዲፈቻ ልጅ እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ሰው ልጅ ይቆጠራል፡፡

## አንቀጽ 9:(3) የተጠበቁ ሁኔታዎች

1. የጉዲፈቻ አድራጊው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች 'ጉዲፈቻውን የሚቃወሙ መሆናቸውን በግልጽ ካስታወቁ ጉዲፈቻው በእነርሱ ላይ እንዳችም ውጤት አያስከትልም፣
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው መቃወሚያ የጉዲፈቻው ውል ከጸደቀበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት በአንድ ውል መዝጋቢ አካል ቀርቦ ካልተመዘገበ ፈራሽ ነው፣
3. ጉዲፈቻ በጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ባልና ሚስት እንዲሁም በልጆቻቸው ላይ የጸና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10. የጉዲፈቻ ልጅ የተፈጥሮ ቤተሰብ

1. የጉድፈቻ ልጅ ከተፈጥሮ ቤተሰቡ ጋር ያለውን የዝምድና መተሳሰር እንደያዘ ይኖራል፣
2. እንዲሁም የጉዲፈቻ ልጅ በሆነው ሰው ባል ወይም ሚስትና ተወላጆች ላይ የዝምድናው መተሳሰር ይጸናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የጋብቻ አፈጻጸም

## አንቀጽ 11. ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓቶች

1. ጋብቻ ጋብቻን ለመመዝገብ በተቋቋመ መንግስታዊ አካል ፊት ሊደረግ ይችላል፣
2. እንዲሁም በሁለቱ ተጋቢ ወገኖች ሃይማኖት ወይም ባገር ልማድ መሰረት የሚደረግ ጋብቻ በሕግ ተቀባይነት አለዉ፡፡

www.abyssinialaw.com



**ዓንቀፅ 12. ብሄራዊ ሓዳር**

ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ክመራዓው ኣብ ቅድሚ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ምስ ቀረቡን እቲ ምዝገባ ሓላፊ ፍቓዶም ሓቲቱ ነቲ ሓዳር ምስ መዝገበ ብሄራዊ ሓዳር ተፈፂሙ ይበሃል፡፡

**ዓንቀፅ 13. ብሃይማኖት ዝፍፀም ሓዳር**

ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ብውሳነኦምን ብስርዓቶምን ክኽም ሃይማኖቶም ወይ ክዓ ካብ ክልቲኦም ብሓዲኦም ሃይማኖት ሓዳር እንትፍፅሙ ዋጋ ዘለዎን ዝፀንዐን ሓዳር ከምዝፈፀሙ ይቑፀር፡፡

**ዓንቀፅ 14. ብልማድ ዓዲ ዝፍፀም ሓዳር**

ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ብከባቢኦም ልማድ ወይ ብናይ ሓዲኦም ልማድ ዓዲ ኣብ መንጎኦም ቀዋሚ ዝኾነ ርክብ ሓዳር ዘስዕብ ስርዓት ፈፂሞም እንትርከቡ ኣብ መንጎኦም ሓዳር ኣሎ ይበሃል፡፡

**ክፍሊ ሓደ**

**ንዝኾነ ስርዓት ሓዳር ዝኾኑ ሓፈሻዊ ኩነታት**

**ዓንቀፅ 15. ፍቓድ**

ዝፀንዕ ሓዳር ተፈፂሙ ዝብሃል ሓደ ወድን ሓንቲ ጓልን ንምምርዓው ነፃን ሙሉእን ፍቓዶም እንትህቡ ጥራሕ'ዩ፡፡

**ዓንቀፅ 16. ዕድመ**

እቲ ወዲ ኮነ እታ ጓል ኣንስተይቲ ዓሰርተ ሸሞንተ ዓመት እንተይመልኦም ሓዳር ምግባር ክልኩል'ዩ፡፡

**ዓንቀፅ 17. ስጋ ዝምድና**

ኣብ መንጎ ስጋ ዝምድና ዘለዎም ሓደ ወድን ሓንቲ ጓልን ሓዳር ምግባር ክልኩል'ዩ፡፡

**ዓንቀፅ 18. ሓዳር ዝምድና**

ኣብ መንጎ ሓዳር ዝምድና ዘለዎም ሓደ ወድን ሓንቲ ጓልን ሓዳር ምግባር ክልኩል'ዩ፡፡

**አንቀጽ 12. ብሄራዊ ጋብቻ**

አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ለማድረግ በጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ ሲቀርቡና የምዝገባ ሓላፊው ፈቃዳቸውን ጠይቆ ጋብቻውን ሲመዘግብ ብሄራዊ ጋብቻው ተፈጸመ ይባላል፡፡

**አንቀጽ 13. የሃይማኖት ጋብቻ**

አንድ ወንድና አንዲት ሴት በውሳኔቸውና በስርአታቸው እንደ የሃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ ባንደኛው ሃይማኖት ጋብቻ ሲፈጽሙ ዋጋ ያለውና የሚጸና ጋብቻ እንደፈጸሙ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 14. በሃገር ልማድ የሚፈፀም ጋብቻ**

አንድ ወንድና አንዲት ሴት በአከባቢያቸው ልማድ ወይም በአንዳቸው የአከባቢ ልማድ በመካከላቸው ቋሚ የሆነ ግንኙነት የሚያስከትል ስርዓት ፈጽመው ሲገኙ በመካከላቸው ጋብቻ አለ ይባላል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ለማንኛውም የጋብቻ ስርዓት የሚሆኑ አጠቃላይ ሁኔታዎች**

**አንቀጽ 15. ፈቃድ**

የሚጸና ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፍቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 16. ዕድሜ**

ወንዱም ሆነ ሴቷ አስራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው፡

**አንቀጽ 17. የስጋ ዝምድና**

የስጋ ዝምድና ባላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው፡፡

**አንቀጽ 18. የጋብቻ ዝምድና**

የጋብቻ ዝምድና ባላቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com





**ዓንቀፅ 19. ተወላድነቱ ብሕጊ ዘይተረጋገፀ ቆልዓ**

ካብ ሓዳር ወፃኢ ዝተወለደ ቆልዓ ተወላድነቱ ብሕጊ ዝተረጋገፀ እንተዘይኾነ'ኳ ተወላድነቱ ብሕብረተሰብ ዝፍለጥ እንተኾይኑ ብመሰረት ዓንቀፅ 17ን 18ን እዚ ሕጊ ሓዳር ንምኽልካል ብቑዕ'ዩ፡፡

**ዓንቀፅ 20. ኣብ ልዕሊ ሓዳር ሓዳር**

ዝኾነ ሰብ ኣቐዲሙ ብሓዳር ዝተኣሰረ እንተኾይኑ፡ እዚ ዝፀንዐ ሓዳር ኣብ ዝሃለወሉ እዋን ካልእ ሓዳር ምግባር ኣይከኣልን ፡፡

**ዓንቀፅ 21. ብወኪል መርዓ ምፍፃም ዘይከኣል ምኻኑ**

1. ተመራዓውቲ መርዓ ኣብ ዝፈፀመሉ ዕለት ብግምባር ተረኺቦም ፍቓደኛነቶም ክህቡ ኣለዎም፡
2. ብቑዕ ምኽንያት ዘጋጠመ ምኻኑ ተፈሊጡ መንግስታዊ ዓቃቢ ሕጊ እንተዘይፈቒዱ መርዓ ብውክልና ምፍፃም ኣይከኣልን፡

**ዓንቀፅ 22. ብፍርዲ ብዛዕባ ዝተኸልከለ ሰብ ሓዳር**

1. ዝኾነ ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ እንድሕር ቤት ፍርዲ ዘይፈቒድሉ ሓዳር ክገብር ኣይኽእልን፡
2. ብዛዕባ'ዚ ጉዳይ ንቤት ፍርዲ ሕቶ ዘቕርብ ባዕሉ እቲ ዝተኸልከለ ሰብ ወይ መመሓዳሪኡ'ዩ፡
3. ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ ውዕሊ ሓዳር ክፍፅም ዝኽእለሉ ስርዓት ኣብ 1952 ዓ.ም ኣብ ዝወፀ ፍታብሄር ሕጊ ኢትዮጵያ ብዛዕባ ክእለት ሰባት ኣብ ዝብል ክፍሊ ብዝተገለፀ መሰረት ይኸውን፡፡

**ዓንቀፅ 23. ብሓይሊ ተግባር ዝተረኸበ ፍቓድ**

1. ብሓይሊ ተግባር ብዝተረኸበ ፍቓድ ዝተፈፀመ ሓዳር ኣይፀንዕን፡
2. ብሓይሊ ተግባር ዝተረኸበ ፍቓድ'ዩ ዝበሃል ባዕሉ ፍቓድ ዝሃበ ሰብ ወይ ወለዱ ወይ ካብ ተወለድቲ ሓደ ወይ ንካልኦት ቀረባ ኣዝማዱ ዝኾኑ ክፍፀሞም ካብ ዝበለ ካብ ክቢድ ሓደጋ ንምድሓን ክብል ፍቓድ ዝሃቦ እንተኮይኑ'ዩ፡፡

**አንቀጽ 19. ተወላጅነቱ በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅ**

ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ ተወላጅነቱ በሕግ ባይረጋገጥም እንኳ በማህበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 17 እና 18 መሰረት ጋብቻን ለመከልከል በቂ ነው፡፡

**አንቀጽ 20. በጋብቻ ላይ ጋብቻ**

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ፡ ይህ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈጸም አይችልም ፡፡

**አንቀጽ 21. ጋብቻን በወኪል መፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ**

1. ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈጸምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃደኝነታቸውን መስጠት አለባቸው፡
2. ብቁ ምክንያት ያጋጠመ መሆኑን ታውቆ መንግስታዊ ዓቃቢ ሕጊ ካልፈቀደ በስተቀር ጋብቻ በወኪል መፈጸም አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 22. በፍርድ ስለተከለከለ ሰው ጋብቻ**

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው፡ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡
2. ስለዚህ ጉዳይ ለፍርድ ቤት ጥያቄ የሚቀርበው የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ነው፡
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው የጋብቻ ውል ሊፈጽም የሚችልበትን ስርዓት በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሃብሄር ሕግ ስለሰዎች ችሎታ በሚል ክፍል በተገለጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 23. በኃይል ተግባር የተገኘ ፍቃድ**

1. በኃይል ተግባር በተገኘ ፈቃድ የተፈጸመ ጋብቻ አይጸናም፡
2. ፈቃድ በኃይል የተገኘው ነው የሚባለው፡ ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወለጆቹ ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነን ሰው ሊፈጸምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com





**ዓንቀፅ 24. መሰረታዊ ስሕተት**

1. ብስሕተት ዝተረኸበ ፍቓድ ዝተፈፀመ ሓዳር ኣይፀንዕን፡
2. ብምኽንያት ስሕተት ፍቓድ ተጓዲሉ ዝበሃል እቲ ስሕተት መሰረታዊ ኮይኑ እንትርከብ'ዩ፡፡
3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (2) ዝተገለፀ ሓፈሻዊ ድንጋገ ሕልው ኮይኑ ዝስዕቡ እንተጋጥሙ መሰረታዊ ስሕተት ከምዝተፈፀመ ይቑፀር፡

ሀ. ኣብ መንነት እቲ ንሓዳር ዝዓሊዩ ሰብ ብምስሕሓቱ ምኽንያት
ክምርዓዎ እየ ኢሉ ምስ ዘይሓሰቦ ሰብ ሓዳር ጌሩ እንትርከብ፡

ለ. እቲ ንሓዳር ዝደለዮ ሰብ ዘይድሕን ክቢድ ሕማም ወይ ካብ ትውልዲ
ናብ ትውልዲ ዝማሓላለፍ ነባሪ ሕማም ዘለዎ ምዃኑ እንተይፈለጠ
ዘእተዎ እንተኾይኑ፡

ሐ. እቲ ሓደ ተማራዓዊ ፆታዊ ርክብ ክፍፅም ዘይኽእል ምዃኑ ብዘይምፍላጡ ምኽንያት ዝተመርዓወ እንተኾይኑ፡

መ. ኣብ ልዕሊ ንሓዳር ዘሓሰብዎ ሰብ ሃይማኖት ዝተሳሓሓተ እንተኾይኑ፡

ረ. እቲ ካሊእ መማራዕወቲ ምስ ተመሳሳሊ ፆታ ርክብ ግብረ ስጋ ምፍፃም ልምዲ ዘለዎ ምዃኑ ብዘይምፍላጥ ምኽንያት ሓዳር ዝገበረ እንተኾይኑ፡፡

**ዓንቀፅ 25. ሰበይቲ ንበይና ብዘይሓዳር ስትነብረሉ ዝተወሰነ ሰዋን**

1. ሓንቲ ሰበይቲ ቅድም ዝነበራ ሓዳር ካብ ዝተረፈሉ ዕለት ጀሚሩ ተስዓ /90/ መዓልትታት እንተይሓለፈ ምስ ካሊእ ሰብ እንደገና ሓዳር ምግባር ኣይትኽእልን ፡
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) ዝተደንገገ ተፈፃሚ ዘይኾውን እታ ሰበይቲ ኣቐዲሙ ካብ ዝነበራ ሓዳር ምስተረፈ ተስዓ (90) ማዓልቲታት እንተይመልአ፡

ሀ. ቆልዓ እንድሕር ወሊዳ፡ ወይ

**አንቀጽ 24. መሰረታዊ ስህተት**

1. በስህተት በተገኘ ፈቃድ የተፈጸመ ጋብቻ አይጸናም፡
2. በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጓደለ የሚባለው ስህተቱ መሰረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተገለጸው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ተፈፃሚ ዘይኾውን፡ እታ ሰበይቲ ቅድም ሆኖ፡ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሰረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል፡

ሀ. በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሳሳቱ ምክንያት አገባዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሰው ያገባ ሲሆን፡

ለ. የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ነዋሪ በሽታ ያለበት መሆኑንም ሳያውቅ ያገባው ሲሆን፡

ሐ. ሌላው ተጋቢ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባ ሲሆን፡

መ. በሚያገባው ሰው ሃይማኖት ላይ የተሳሳተ ሲሆን፡

ሠ. ሌላው ተጋቢ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የመፈጸም ልማድ ያለው መሆኑን ባለማወቅ ምክንያት ያገባ ሲሆን፡፡

**አንቀጽ 25. ሴት በብቸኝነት ያለትዳር የምትኖርበት የተወሰነ ጊዜ**

1. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ ዘጠና /90/ ቀናት ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈጻሚ የማይሆነው፡ ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ ዘጠና (90) ቀናት ሳይሞላ፡

ሀ. ልጅ የወለደች እንደሆነ ፡ ወይም

www.abyssinialaw.com





ለ. እትፍፅሞ ሓዳር ምስ ናይ ቀደም ሰብኣያ እንተኾይኑ፣ ወይ

ሐ. ጥንስቲ ዘይምኳና ብሓኪም እንትረጋገፅ ፡ ወይ

መ. በይና ክትነብር ዝተወሰነ እዋን ከይትፅበ ቤት ፍርዲ እንትውስን፡፡

## ክፍሊ ክልተ

## ሓዳር ከይፍፀም ብዛዕባ ምቅዋም

### ዓንቀፅ 26. ብዛዕባ ምቅዋም

ሓዳር ንምፍፃም ኣድላይቲ ዝኾኑ ኩነታት ኣይተማልኡን ብምባል ክፍፀም ንዝተሓሰበ ሓዳር ከይፍፀም ምቅዋም ይከኣል፡፡

### ዓንቀፅ 27. ምቅዋም ብዛዕባ ዝኽእሉ ወገናት

ሓዳር ከይፍፀም ምቅዋም ዝኽእሉ ወገናት ዝስዕቡ ጥራሕ'ዮም፡-

1. እቲ ዝቐርብ ተቓውሞ ብምኽንያት ዕድመ እንተኾይኑ ወለዲ፣ ዓቃቢ ሕጊ ወይ ካልኦት የእትወና'ዩ ዝብሉ ሰባት፣
2. እቲ ዝቐርብ ተቓውሞ ብምኽንያት ስጋ ወይ ሓዳር ዝምድና እንተኾውን ናብ ላዕሊ ዝቑፀሩ ናይ ተማራዓውቲ ወይ ናይ ሓዲኦም ወለዲ፣ 18 ዓመት ዝመልኦም ኣሕዋት ወይ ኣሓት ወይ ዓቃቢ ሕጊ፣
3. እቲ ዝቐርብ ተቓውሞ ብምኽንያት ኣብ ርእሲ ሓዳር ሓዳር ምፍፃም እንተኾይኑ ምስቲ ካልእ ሓዳር ዝፍፅም ሰብ ስሩዕ ሓዳር ኣለኒ ዝብል ሰብ ወይ ዓቃቢ ሕጊ፣
4. እቲ ዝቐርብ ተቓውሞ ብምኽንያት ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ እንተኾይኑ መማሓደሪኡ ወይ ዓቃቢ ሕጊ፣

### ዓንቀፅ 28. ተቓውሞ ዝቐርበሉ ስርዓትን እዋንን

1. ሓዳር ከይፍፀም ዝቐርብ ተቓውሞ ብፅሑፍ ኮይኑ ኣዝዩ እንተደንጒዩ እቲ መርዓ ካብ ዝፍፀመሉ ዕለት ቅድሚ 15 መዓልቲ ናብ መርዓ ውዕሊ መፈፀሚ ኣካል ክቐርብ ኣለዎ፣

ለ. ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ. እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ.በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

### አንቀጽ 26. ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈጸም የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈጸም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል፡፡

### አንቀጽ 27. መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈጸም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው፣

1. የሚቀርበው ተቃውሞ በዕድሜ ምክንያት ሲሆን ወላጆች፣ ዓቃቢ ሕግ ወይም ሌላ ማናቸውም ያገባናል የሚሉ ሰዎች፣
2. የሚቀርበው ተቃውሞ በስጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን፣ የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ 18 ዓመት የሞላቸው ወንድሞች ወይም እህቶች ወይም ዓቃቢ ሕግ፣
3. የሚቀርበው ተቃውሞ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈጸም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ተጋቢ ወይም ዓቃቢ ሕግ፣
4. የሚቀርበው ተቃውሞ በፍርድ በተከለከለ ሰው ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዓቃቢ ሕግ፣

### አንቀጽ 28. ተቃውሞ ስለሚቀርብበት ስርዓትና ጊዜ

1. ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚቀርበው ተቃውሞ በጽሑፍ ሆኖ እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ከ15 ቀን በፊት ለጋብቻ ውል አስፈጻሚ አካል መቅረብ አለበት፣

www.abyssinialaw.com

2. ውዕሊ ሓዳር መፈፀሚ ኣካል ኣብቲ ዝቐረበ ተቓውሞ ቅድሚ ውሳነ ምሃቡ ሪኢቶ ተማራዓውቲ ክቕበል ኣለዎ፡፡

**ዓንቀፅ 29. ኣብ ዝቐረበ ተቓውሞ ዝውሃብ ውሳነ**

1. ሓዳር ዘፈፅም ኣካል ኣብ ልዕሊ ዝቐረበ ተቓውሞ ኣብ ውሽጢ ሓሙሽተ መዓልቲ ውሳነ ክሀብ ኣለዎ፡
2. ሓዳር ዘፈፅም ኣካል ንዝቐረበ ተቓውሞ ብዘይምቕባል መርዓ ክፍፀም ዝሀቦ ውሳነ ናይ መወዳእታ ይኸውን፡
3. ሓዳር ዘፈፅም ኣካል ነቲ ዝቐረበ ተቓውሞ እንተተቐቢሉዎ ሓዳር ከይፈፀም ክገብር ኣለዎ፡
4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (3) ዝተመልከተ ውሳነ ዝሃበ ኣካል ንውሳኒኡ ምኽንያት ዝገበሮም ነጥብታት ሽዑ ንሽዑ ተማራዓውቲ ክፈልጡዎም ክገብር ኣለዎ፡፡

**ዓንቀፅ 30. ብዛዕባ ይግባይ**

1. ኣብዚ ሕጊ ዓንቀፅ 29 ንኡስ ዓንቀፅ 3 ኣብ ዝተመልከተ ኩነታት ኣብ ዝውሃብ ውሳነ ተማራዓውቲ ወይ ካብ ተማራዓውቲ ሓዲኦም ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ይግባይ ምቕራብ ይኽእሉ፡
2. ይግባኣኒ ዝቐረበሉ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ነቲ ኣብዚ ሕጊ ዓንቀፅ 29 ንኡስ ዓንቀፅ 3 ዝተመልከተ ዝተውሃበ ውሳነ እንተስዒሩዎ ሓዳር ኣፈፃሚ ኣካል ነቲ ሓዳር የፈፅም፡

**ክፍሊ ሰለስተ**

**ብሄራዊ መርዓ**

**ዓንቀፅ 31. ስልጣን ዘለዎ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ**

ካብቶም ተማራዓውቲ ሓደ ወይ ካብ ተማራዓውቲ ወለዲ ወይ ካብ ቀረባ ኣዝማድ ሓደ ቅድሚ መርዓ ዝግበረሉ ዕለት እንተወሓደ ክየቋረፀ ንሽዱሽተ ወርሒ ኣብ ዝነብረሉ ቦታ ኣብ ዝርከብ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ እቲ ሓዳር ይፍፀም፡፡

2. የጋብቻ ውል አስፈጻሚው አካል በተቃወሞው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 29. በቀረበው ተቃውሞ ላይ ስለሚሰጠው ውሳኔ**

1. ጋብቻ የሚያስፈጽም አካል በሚቀርብለት ተቃውሞ ላይ በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡
2. ጋብቻ አስፈጻሚው አካል ተቃውሞውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈጸም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡
3. ጋብቻ አስፈጻሚው አካል ተቃውሞውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ አለበት፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ውሳኔ የተሰጠው አካል ለውሳኔው ምክንያት ያደረጋቸውን ነጥቦች ተጋቢዎቹ ወዲያውኑ እንዲያውቋቸው ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 30 ስለይግባኝ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 3 በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዳቸው ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡
2. ይግባኝ የቀረበለት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት በአንቀፅ 29 ንኡስ ኣንቀፅ (3) በተመለከተ የተሰጠን ውሳኔ የጋብቻ አስፈጻሚውን አካል የሻረው እንደሆነ ጋብቻ ኣስፈፃሚ ኣካሉ ጋብቻውን ያስፈጽማል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ብሄራዊ ጋብቻ**

**አንቀጽ 31. ስልጣን ያለው የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ**

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ ፊት ይፈጽማል፡፡

www.abyssinialaw.com



**ዓንቀፅ 32. ንዘይምምርዓው ዝግበር ውዕል**

1. ሓደ ሰብ ሓዳር ኣይገብርን እየ ወይ ድማ ደጊመ ሓዳር ኣይገብርን ኢሉ/ላ ቃል ምእታው ብሕጊ ውፅኢት የብሉን፣
2. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ'ውን ኣብዚ ኣንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1 ዘሎ ዋኒን ኣይምልከቶን፡፡

**ዓንቀፅ 33. ሓዳር ከይፈፀም ብዛዕባ ምኽልካል**

1. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኩነታት ሓዳር ብዝግባእ ከምዝተፈፀመ የረጋግፅ፣
2. ሓዳር ከይፍፀም ዝኽልክል ብቑዕ ምኽንያት ከም ዘሎ እንድሕር ፈሊጡ ሓዳር ከይገብሩ ይኽልክሎም፣
3. እዚ ኣብ ዝኾነሉ እዋን ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ነቶም ሓዳር ክገብሩ ዝደልዩ ጓል ኣንስተይትን ወዲ ተባዕታይን ዝተኽልከሉሉ ምኽንያት ይገልፀሎም፡፡

**ዓንቀፅ 35. ኣብ ባዕሊ ንዝተገበረ ክልከላ ዝቐርብ ጥርዓን**

1. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ብዝገብሮ ክልከላ ካብ ተማራዓውቲ ሓዲኦም ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥርዓን ክቕርቡ ይኽእሉ፡፡ እቲ ቤት ፍርዲ ድማ ብዛዕባ እቲ ክልከላ ውሳነ ይህብ፣
2. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እቲ ክልከላ ዘይግቡእ'ዩ ኢሉ ውሳነ እንተዕሪፍሉ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ብዝኾነ ምኽንያት እቲ መርዓ ከይፍፀም ክኽልክል ኣይኽእልን፡፡

**ዓንቀፅ 36. ሓዳር ዝፈፀመሉ ዕለት ብዛዕባ ምውሳን**

ሓዳር ዝፈፀመሉ መዓልቲ ብስምምዕ እቶም ተማራዓውቲ ይውሰን፡፡

**ዓንቀፅ 37. ብዛዕባ ኣፈፃፅማ ሓዳር ምፍላጥ**

1. ሓዳር በቶም ዝመራዓዉ ወገናት ኣብ ቅድሚ ብነብሲ ወከፎም ዝቐርቡ ክክልተ መሰኻኽር ብግልፂ ይፍፀም፣



**አንቀጽ 32. ላለመጋባት የሚደረግ ውል**

1. አንድ ሰው አላገባም ብሎ ወይም ዳግም አላገባም ብሎ ቃል ቢገባ በህግ ውጤት የለውም፣
2. የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛም በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ያለው ነገር አይመለከተውም፡፡

**አንቀጽ 33 ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመከልከል**

1. የጋብቻ መዝገቢ ሰራተኛ የጋብቻው ሁኔታዎች በሚገባ የተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣል፣
2. ጋብቻው እንዳይፈጸም የሚከለክል በቂ ምክንያትን መኖሩን ካወቀ ጋብቻውን እንዳይፈጸም ይከለክላቸዋል፣
3. እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ የጋብቻ መዝጋቢው ሰራተኛ ጋብቻን ለመፈጸም ለሚፈልጉት ሴትና ወንድ የተከለከሉበትን ምክንያት ይገልጽላቸዋል፡፡

**አንቀጽ 35. እሳይ በተደረገው ክልከላ የሚቀርብ አቤቱታ**

1. የጋብቻ መዝጋቢው ሰራተኛ ባደረገው ክልከላ ላይ ከተጋቢዎቹ አንዳቸው ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም ስለዚህ ክልከላ ውሳኔ ይሰጣል፣
2. ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ክልከላው ያለአግባብ መሆኑን የወሰነ እንደሆነ የጋብቻ መዝገቢው ሰራተኛ በማናቸውም ምክንያት ጋብቻው እንዳይፈጸም ሊከለክል አይችልም፡፡

**አንቀጽ 36. ጋብቻው የሚፈጸምበትን ቀን ስለመወሰን**

ጋብቻው የሚፈጸምበት ቀን በተጋቢዎች በስምምነት ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 37. የጋብቻ አፈጻጸም ስለማሳወቅ**

1. ጋብቻው ሁለት ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈጽማል፣

www.abyssinialaw.com



2. ምስክራት÷ ኣዝማድ ተማራዓውቲ ወይ ካልኦት ሰባት ክኾኑ ይኽእሉ'ዮም፡፡

### ዓንቀፅ 38. ስርዓት ኣፈፃፅማ ሓዳር

1. ምስክራት ሓዳር ዝኽልክል ምኽንያት ምህላው ኣይንፈልጥን ኢሎም ማሓላ ቃሎም ክህቡ ኣለዎም፡
2. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ካብቶም ዝመራዓው ጓል ኣንስተይቲን ወዲ ተባዕታይን በቢተራ ንምምርዓው ከምዝፈቐዱ ቃል ክቕበል ኣለዎ፡
3. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ትሕቲ ስልጣኑ ንዝኾነ ጉዳይ ብስም ሕጊ ብሓዳር ዝተ ሳሰሩ ከምዝኾኑ ኣፋሊጡ ሽው ንሽው ናይ ሓዳር ምስክር ወረቀት ይህቦም፡፡

### ክፍሊ ኣርባዕተ
### ኣፈፃፅማ ካልኦት ስርዓታት ሓዳር

### ዓንቀፅ 39. ብሃይማኖት ብዛዕባ ዝፍፀም ስርዓት ሓዳር

1. ብሃይማኖት ዝፍፀም ሓዳር ዝፍፀመሉ ኩነታትን ዓይነት ኣፈፃፅምኡን ከምቲ ሃይማኖቲ ዝፈቐዶ ኮይኑ ይውሰን፡
2. ኣብዚ ሕጊ ውሽጢ ብዛዕባ ምዝገባ ሓዳር ኣብ ዝብል ካብ ዓንቀፅ 141 ክሳብ 149 ዝተደንገገ መሰረት ብምግባር ምስክር ወረቐት ምዝገባ ሓዳር ምውሃእ ይግባእ፡

### ዓንቀፅ 40. ብልማዳዊ ብዛዕባ ዝፍፀም ስርዓት ሓዳር

1. ልማዳዊ ሓዳር ክፍፀም ዝኽእለሉ ኩነታትን ስርዓት ኣፈፃፅምኡን ብመሰረት ናይቲ ከባቢ ልምዲ ስርዓት ኣፈፃፅማ ይውሰን፡፡
2. ኣብዚ ሕጊ ውሽጢ ብዛዕባ ምዝገባ ሓዳር ኣብ ዝብል ካብ ዓንቀፅ 143 ክሳብ ዓንቀፅ 151 ብዝተደንገገ መሰረት ምስክር ወረቐት ምዝገባ ሓዳር ምውሃእ ይግባእ፡፡



2. ምስክሮች የተጋቢዎቹ ዘመዳሞች ወይም ሌሎች ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### አንቀጽ 38. የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት

1. ምስክሮች ጋብቻን የሚከለክል ነገር መኖሩን እናውቅም ብለው በመሓላ ቃላቸውን መስጠት አለባቸው፡
2. ጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛው ከሴትና ወንድ ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸም መፍቀዳቸውን በየተራ ቃል መቀበል አለበት፡
3. ጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛው በስልጣኑ ውስጥ ለሆኑ ጉዳይ በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ወዲያውኑ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

### ክፍል አራት
### ሌሎች የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓቶች

### አንቀጽ 39. በሃይማኖት ስርዓት የሚፈጸም ጋብቻ

1. ጋብቻ በሃይማኖት ስርዓት መሰረት ሊፈጸም የሚችልበት ሁኔታዎችና የአፈጻጸሙ ዓይነት እንደየሃይማኖቱ ይወሰናል፡
2. በዚህ ሕግ ውስጥ ስለጋብቻ ምዝገባ በሚለው ከአንቀጽ 143-151 በተደነገገው መሰረት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ማውጣት ይገባል፡፡

### አንቀጽ 40. በልማዳዊ ስርዓት ስለሚፈጸም ጋብቻ

1. ጋብቻ በልማዳዊ ስርዓት መሰረት ሊፈጸም የሚችልበትን ሁኔታዎችና የአፈጻጸሙ ስርዓት እንደየአከባቢው ልማድ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ ሕግ ውስጥ ስለጋብቻ ምዝገባ በሚለው ከአንቀጽ 143 እስከ አንቀጽ 151 በተደነገገው መሰረት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ማውጣት ይገባል፡፡

www.abyssinialaw.com



## ምዕራፍ ሰለስተ

## ስርዓታት ሓዳር ብዘይምኽባር ዝውሃብ መቕፃዕቲ

### ክፍሊ ሓደ

### ንኹሉ ዓይነታት ሓዳር ዝኸውን ሓፈሻዊ ስርዓት

**ዓንቀፅ 41. ዕድመ (1) ገበን መቕፃዕቲ**

1. ዕድመ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይቲን ካብ 18 ዓመት ንታሕቲ ምዃኖም እንዳፈለጠ ወይ ክፈልጥ እንዳተገበኦ ስርዓት ሓዳር ክፍፀም ዝገበረ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፥
2. ክልቲኦም ተማራዓውቲ ዕድሚኦም ካብ 18 ዓመት ንታሕቲ ምዃኖም እንዳፈለጡ ኣብቲ ሓዳር ምስክርነቶም ዝሃቡ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፡፡

**ዓንቀፅ 42. ምፍራስ ሓዳር (2)**

1. ኣብ ዓንቀፅ 41 እዚ ሕጊ ብዝተገለፀ ኩነታት ዝተፈፀመ ሓዳር ብዝኾነ ሕቶ በዓል ጉዳይ ወይ ኣኽባሪ ሕጊ ይፈርስ፡፡
2. ሕጊ ብዘገድዶ መሰረት ንሓዳር ዝተወሰነ ዕድመ ተማሊኡ እንትርከብ ሓዳር ክፈርስ ጥርዓን ክቐርብ ኣይኽእልን፡፡

**ዓንቀፅ 43. ብስጋ ወይ ብሓዳር ዝምድና (1) ምፍራስ ሓዳር**

ብስጋ ወይ ብሓዳር ዝምድና ዘሎ ክልከላ ብምጥሓስ ሓዳር ተፈፂሙ እንትርከብ ዝኾነ በዓል ጉዳይ ወይ ብዓቃቢ ሕጊ ብዘቕርቦ ጥርዓን እቲ ሓዳር ክፈርስ ይግበር፡፡

**ዓንቀፅ 44.(2) መቕፃዕቲ**

1. ብስጋ ወይ ብሓዳር ዝምድና ምኽንያት ዝኸልክል ነገር ከምዘሎ እንዳፈለጠ ወይ ክፈልጥ እንዳተገበኦ ኣብ መንጎ ክልቲኦም ተማራዓውቲ ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፡፡



## ምዕራፍ ሶስት

## የጋብቻ ስርዓቶች ባለማክበር የሚሰጥ ቅጣት

### ለሁሉም የጋብቻ ዓይነቶች የሚሆን ጠቅላላ ስርዓት

**አንቀጽ 41. ዕድሜ (1) የወንጀል ቅጣት**

1. የወንድና ሴት ተጋቢዎቹ ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በታች መሆኑ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጋብቻ ስርዓት እንዲፈጸም ያደረገ የጋብቻ መዝገቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡
2. የሁለቱም ተጋቢዎች ዕድሜ ከ18 ዓመት በታች መሆኑን እያወቁ በጋብቻው ምስክርነታቸው የሰጡ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፡፡

**አንቀጽ 42. የጋብቻው መፍረስ**

1. የዚህ ሕግ አንቀጽ 41 በተገለጸው አኳኋን የተፈጸመ ጋብቻ በማናቸውም ባለጉዳይ ወይም በሕግ አስከባሪ ጥያቄ ይፈርሳል፡
2. ሕግ በሚያስገድደው መሰረት ለጋብቻ የተወሰነው ዕድሜ ተሟልቶ የተገኘ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ አቤቱታ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 43. የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና (1) የጋብቻ መፍረስ**

በስጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ያለውን ክልከላ በመተላለፍ ጋብቻ ተፈጽሞ ሲገኝ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም አቃቤ ሕግ በሚያቀርበው አቤቱታ ጋብቻው እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 44. (2) ቅጣት**

1. በስጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት የሚከለክል ነገር መኖሩን እያወቀ ወይም ይህን ሁኔታ ማወቅ ሲገባው በሁለት ተጋቢዎች መካከል ጋብቻን ያስፈጸመ ባለስልጣን ወይም ጋብቻ መዝገቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡

www.abyssinialaw.com



2. ከምኡ'ውን ስጋ ዝምድና ወይ ብሓዳር ምትእስሳር ምህላው እንዳፈለጡ ወይ ክፈልጡ ዝግበኦም ተማራዓውትን ኣብቲ ሓዳር ምስክር ዝኾኑ ሰባትን ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፣
3. እዚ ቅፅዓት ዝፍፀም ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ነቲ ሓዳር እንተፍሪስዎ እዩ፣

ዓንቀፅ 45. ኣብ ርእሲ ሓዳር ዝግበር ሓዳር

(1) መቕፃዕቲ

1. ቅድም ኢሉ ብሓዳር ዝተኣሰረ ምዃኑ እንዳፈለጠ ወይ ክፈልጥ እንዳተገበኦ ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣
2. ከምኡውን እዚ ኩነታት እንዳፈለጡ ወይ ክፈልጡ እንዳተገበኦም ሓዳር ዝገበሩ ተማራዓውትን ምስክር ዝኾኑ ሰባትን ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፡፡

ዓንቀፅ 46. (2) ምፍራስ ሓዳር

1. ኣብ ልዕሊ ሓዳር ሓዳር ዝተፈፀመ ምዃኑ እንትረጋገፅ ብተበዳሊ ወይ ብዓቃቢ ሕጊ ብዝቐርብ ጥርዓን መሰረት እቲ ሓዳር ይፈርስ፣

2. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እቲ ሓዳር ክፈርስ ዝገብር ኣብ ርእሲ ሓዳር ሓዳር ኣብ ዝተፈፀመሉ እዋን ብዘየጠራጥር ኩነታት በዓል ሓዳር ወይ በዓልቲ ሓዳር ብህይወት ከምዝነበረ ወይ ከምዝነበረት ክረጋገፅ እንከሎ እዩ፡፡

ዓንቀፅ 47. (3) ብዛዕባ መርትዖ

መርትዖ ከቕርብ ዘለዎ እቲ ኣብ ርእሲ ሓዳር ሓዳር ተፈፂሙ ዝብል ወገን እዩ፡፡

ዓንቀፅ 48. ሓዳር ክፍፅም ክእለት ዘይብሉ ሰብ

(1) መቕፃዕቲ

1. ብኣእምሮ ምንዋፅ ዝተኸልከለ ወይ ትሕቲ ዕድመ ምዃኑ እንዳፈለጠ ወይ ምፍላጥ እንዳተገበኦ ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣



2. እንዲሁም የስጋ ዝምድና ወይም በጋብቻ መተሳሰር መኖሩን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ተጋቢዎችና ለጋብቻው ምስክር የሆኑት ሰዎች በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፣
3. ይህ ቅጣት የሚፈጸመው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ጋብቻውን ካፈረሰው ነው፡፡

አንቀጽ 45. በጋብቻ ላይ የሚፈፀም ጋብቻ

(1) ቅጣት

1. ቀደም ሲል በጋብቻ የታሰረ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ጋብቻውን ያስፈጸመ ባለስልጣን ወይም ጋብቻ መዝገቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፣
2. እንዲሁም ይህን ሁኔታዎች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ጋብቻ የፈጸሙ ተጋቢዎችና ምስክሮች የሆኑ ሰዎች በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፡፡

አንቀጽ 46.(2) የጋብቻው መፍረስ

1. በጋብቻ ላይ ጋብቻ የተፈጸመ መሆኑን ሲረጋገጥ በተበዳዩ ወይም በአቃቤ ሕግ በሚቀርብ አቤቱታ መሰረት ጋብቻው ይፈርሳል፣
2. ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያደርገው በጋብቻ ላይ ጋብቻ በተፈጸመበት ጊዜ በማያጠራጥር አኳኋን ባለትዳሩ ወይም ባለትዳሯ በህይወት እንደነበረ ወይም እንደነበረች ሲረጋገጥ ነው፡፡

አንቀጽ 47. ስለማስረጃ

ማስረጃ ማቅረብ ያለበት በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሟል የሚል ወገን ነው፡፡

አንቀጽ 48. ጋብቻ ሊፈጽም ችሎታ የሌለው ሰው

(1) ቅጣት

1. በአእምሮ መናወጥ የተከለከለውን ወይም ከጋብቻ ዕድሜ በታች መሆኑን እያወቀ ወይም እንዲያውቅ እየተገባው ጋብቻ ያስፈጸመ ባለስልጣን ወይም ጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፣

www.abyssinialaw.com





2. ክምኡ'ውን ምስ ትሕቲ ዕድመ ዝኾነ ወይ ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ ሓዳር ዝገብሩ ወይ ነዚ ሓዳር ምስክር ዝኾኑ ሰባት ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፡፡

**ዓንቀፅ 49./2/ ምፍራስ ሓዳር**

1. ሓዳር ክፈርስ ንዳያኑ ክሓትት ዝኽእል እቲ ትሕቲ ዕድመ ዝኾነ ሰብ ወይ ብኣእምሮ ምንቃፅ ምኽንያት ሓዳር ዝተኸልከለ ሰብ ወይ መማሓዳሪኡ'ዩ፡
2. ክእለት ዝሰኣነ ሰብ ሓዳሩ ክፈርስ ዘቕርቦ ጥርዓን ክእለት ምስኣኑ ምስኣቋረፀ ድሕሪ ሽዱሽተ ወርሒ ክቐርብ ኣይኽእልን፡
3. ብዛዕባ እዚ ዋኒን ካልኦት ሰባት ዘቕርብዎ ጥርዓን ሓዳር ክምዝተፈፀመ ካብ ዝፈለጡሉ ዕለት ጀሚሩ ካብ ሽዱሽተ ወርሒ ንደሓር ክምኡ'ው እቲ ትሕቲ ዕድመ ዘሎ ሰብ ወይ ዝተኸልከለ ሰብ ብኻልእ ብዝኾነ ይኹን ምኽንያት ክእለት ምስኣኑ ምስ ኣቋረፀ ክቐርብ ኣይኽእልን፡፡

**ዓንቀፅ 50. ብሓይሊ ተግባር ዝተለዓለ ጉድለት (1) መቕፃዕቲ**

1. ብሓይሊ ተጠቒሞም ሓደ ሰብ ሓዳር ክፈቅድ ዝገበሩን ነዚ ሓዳር ክፍፀም ምስክር ዝኾኑ ሰባትን ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፡
2. ክምኡ'ውን እዚ ኩነታት እንዳፈለጠ ወይ ክፈልጥ እንዳረገበአ ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተመልከቱ መቕፃዕቲታት መሰረት ይቕፃዕ፡፡

**ዓንቀፅ 51. ምፍራስ ሓዳር (1)**

ዝኾነ ሰብ ብሓይሊ ተገዲዱ ሓዳር ዝገበረ እንተኮይኑ ኣብ ዝኾነ እዋን ሓዳር ንክፈርስ ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ክጠርዕ ይኽእል፡፡

**ዓንቀፅ 52. ስሕተት**

ብዝኾነ ሰብ ካብ ቀንዲ ስሕተት ተላዒሉ ሓዳር ዝገበረ እንተኾይኑ ኣብ ዝኾነ እዋን ሓዳር ክፈርስሉ ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ክጠርዕ ይኽእል፡፡

2. እንዲሁም ከጋብቻ ዕድሜ በታች የሆኑ ወይም በፍርድ ከተከለከለው ሰው ጋር ጋብቻ የፈጸሙ ወይም ለጋብቻው ምስክር የሆኑት ሰዎች በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፡፡

**አንቀጽ 49.(2) የጋብቻ መፍረስ**

1. ጋብቻው እንዲፈርስ ዳኞችን መጠየቅ የሚችለው ከጋብቻ ዕድሜ በታች የሆነው ሰው ወይም በአእምሮ መናወጥ ምክንያት ጋብቻ የተከለከለ ሰው ወይም አሳዳሪው ነው
2. ችሎታ ያጣ ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው አቤቱታ ችሎታ ማጣቱ ከተቋረጠ ከስድስት ወር በኋላ ሊቀርብ አይችልም፡
3. ስለዚህ ጉዳዩ ሌሎች ሰዎች የሚያቀርቡት አቤቱታ ጋብቻ መፈጸሙን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ እንዲሁም ከጋብቻ ዕድሜ በታች ካለው ሰው ወይም ጋብቻ የተከለከለው ሰው በሌላ በማንኛውም ምክንያት ችሎታ ማጣቱን ካቋረጠ በኋላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 50. ከኃይል ተግባር የተነሳ ጉድለት (1) ቅጣት**

1. ሃይል ተጠቅመው አንድ ሰው ጋብቻን እንዲፈቅድ ያደረጉና ይህ ጋብቻ እንዲፈጸም ምስክር የሆኑ ሰዎች በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፡
2. እንዲሁም ይህን ሁኔታ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ጋብቻ እንዲፈጸም ያደረገ ባለስልጣን ወይም የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተመለከቱት ቅጣቶች መሰረት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 51. የጋብቻ መፍረስ**

ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ጋብቻ ያደረገ እንደሆን በማንኛውም ጊዜ ጋብቻው እንዲፈርስ ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል ፡፡

**አንቀጽ 52. ስህተት**

ማንኛውም ሰው ከመሰረታዊ ስህተት የተነሳ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ በማንኛውም ጊዜ ጋብቻው እንዲፈርስለት ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com



## ዓንቀፅ 53. ምቅዋም

1. ኣብ ልዕሊ ሓዳር ዝቐረበ ግቡእ መቃወሚ ብምቅሳል ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣
2. ኣብዚ ኣንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1 ብዝተመልከተ መሰረት ንምምርዓው ፍቓደኛታት ዝኾኑ ዕድሚኦም ካብ ዓሰርተ ሾሞንተ ዓመት ንላዕሊ ዝኾኑ ተማራዓውትን መሰኻኽርምን ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፣
3. ኣብ ልዕሊ እቲ ሓዳር ዝቐረብ መቃወሚ ዋጋ ኣይተውሃበን ብዝብል ምኽንያት ጥራሕ እቲ ሓዳር ንኽፈርስ ክውሰን ኣይኽእልን፡፡

## ዓንቀፅ 54. ብብሕቲ ንምንባር ዝተወሰነ እዋን ብዛዕባ ዘይምሕላው

1. ንብሕታ ንምንባር ዝተወሰነላ እዋን ዘይወደአት ሰበይቲ ተቐቢሉ ሓዳር ዘፈፀመ በዓል መዚ ወይ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣
2. ኣብዚ ኣንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1 ብዝተጠቀሰ መሰረት ሓዳር ክፍፅሙ ፍቓደኛ ዝኾኑ ተመራዓውትን መሰኻኽርምን ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፅዑ፣
3. በይንኻ ንምንባር ዝተወሰነ እዋን ኣይተኸበረን ብዝብል ምኽንያት ጥራሕ ሓዳር ንኽፈርስ ክእዘዝ ኣይክኣልን፡፡

### ክፍሊ ክልተ

### ብሄራዊ ሓዳር

## ዓንቀፅ 55. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ስልጣን ዘይብሉ ምኻኑ

1. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ዓንቀፅ 31 እዚ ሕጊ ዝተቐመጡ ኩነታት ዘይተማለአ ምኻኑ እናፈለጠ ወይ ክፈልጥ እንዳተገበአ ተቐቢሉ ሓዳር ዘፈፀመ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣
2. ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ክምዝግብ ስልጣን ኣይነበሮን ብዝብል ጥርዓን ጥራሕ ሓዳር ይፍረስ ዝብል ውሳነ ክውሃብ ኣይክኣልን፡፡



## አንቀጽ 53. መቃወም

1. በጋብቻው ላይ የተደረገውን ተገቢ መቃወሚያ በማቃለል ጋብቻውን ያስፈጸመ ባለስልጣን ወይም የጋብቻ መዝገቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፤
2. በዚህ ኣንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት ለመጋባት ፍቃደኛ የሆኑት ዕድሚያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆኑት ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፥
3. በጋብቻው ላይ ለቀረበው መቃወሚያ ዋጋ አልተሰጠውም በሚለው ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም፡፡

## አንቀጽ 54. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ

1. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ ያልጨረሰች ሴት ተቀብሎ ጋብቻን ያስፈጸመ ባለስልጣን ወይም የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡
2. በዚህ ኣንቀፅ ንኡስ ኣንቀጽ 1 በተጠቀሰው መሰረት ጋብቻ ለመፈጸም ፍቃደኛ የሆኑት ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣሉ፣
3. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊታዘዝ አይችልም፡፡

### ክፍል ሁለት

### ብሄራዊ ጋብቻ

## አንቀጽ 55. የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 31 ላይ የተቀመጡትን ሁኔታዎች አለመሟላታቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ተቀብሎ ጋብቻ ያስፈጸመ የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡
2. የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ ሊመዘግብ ስልጣን አልነበረውም በሚል አቤቱታ ብቻ ጋብቻ ይፍረስ የሚል ውሳኔ ሊሰጥ አይቻልም፡፡

www.abyssinialaw.com



ዓንቀፅ 56. ንስርዓታት ዘይምሕላው

1. ስርዓታት ኣፈፃፅማ ሓዳር ዘይሓለወ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ኣብ ገበን ሕጊ ብዝተደንገገ መሰረት ይቕፃዕ፣
2. ኣብ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ብዘሎ ምኽንያት ጥራሕ ሓዳር ንኽፈርስ ክውሰን ኣይክኣልን፡፡

ክፋል ሰለስተ

ክስእት ሓዳራት

ዓንቀፅ 57. ፈራስነት

1. ብሃይማኖት ወይ ብልማዳዊ ክፍፀሙ ዝግበኦም ዝነበሩ ኣድለይቲ ዝኾኑ ኩነታት ወይ ስርዓታት ብዘይምፍፃም ምኽንያት ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ነቲ ሓዳር ክፍርሶ ኣይኽእልን፣

2. ኣብ ልዕሊ ልማዳዊ ሓዳር ብሽማግለታት ዓዲ ዝግበር ምስዓር ወይ ምፍራስ ኣብ ቅድሚ ሕጊ ተቐባልነት የብሉን፡፡

ምዕራፍ ኣርባዕተ

ውፅኢት ሓዳር

ክፋል ሓደ

ሓፈሻዊ ስርዓታት

ዓንቀፅ 58. ማዕርነት ዝተፈላለዩ ዓይነታት ሓዳር

ብዝኾነ ዓይነት ስርዓት ዝተፈፀመ ሓዳር ብሕጊ ማዕረ ውፅኢት ኣለዎ፡፡

ዓንቀፅ 59. ፆታዊ ርክብ ምፍፃም

ሓዳር ንዘስዕቦ ውፅኢት ፆታዊ ርክብ ምፍፃሙ ወይ ተፈፂሙ እዩ ኢልካ ምግማት ኣድላዪ ኣይኮነን፡፡

ዓንቀፅ 60. ሓዳር ውዕሊ

1. ሰብ ሓዳር ሓዳሮምን ሃብቶምን ብዝምልከት ቅድሚ ምምርዓዎም ወይ ኣብ ዕለቱ ብውዕሊ ክሰማምዑ ይኽእሉ'ዮም፣

2. ከምኡ'ውን ኣብቲ ዝገብርዎ ውዕሊ ብዛዕባ ኣብ መንጎኦም ዘሎ ርክብ እቲ ሓደ ነቲ ሓደ ክገብሮ ዘለዎ ግቡእን ክረኽቦ ዝግባእ መሰልን ክገልፁ ይኽእሉ'ዮም፡፡



አንቀጽ 56. ስርዓቶችን ስላለመጠበቅ

1. የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓቶችን ያልጠበቀ ጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በወንጀል ሕግ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፣
2. በንኡስ አንቀፅ 1 ባለ ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይቻልም፡፡

ክፍል ሶስት

ሴሉች ጋብቻዎች

አንቀጽ 57. ፈራሽነት

1. በሃይማኖት ወይም በልማዳዊ ሊፈጸሙ የሚገባቸው የነበሩ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ስርዓቶች ባለመፈጸማቸው ምክንያት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ጋብቻውን ሊያፈርሰው አይችልም፣
2. በልማዳዊ ጋብቻ ላይ በአገር ሽማግሌዎች የሚደረግ መሻር ወይም ማፍረስ በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም፣

ምዕራፍ አራት

የጋብቻ ውጤት

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ስርዓቶች

አንቀፅ 58. የልዩ ልዩ የጋብቻ ዓይነቶች እኩልነት

በማናቸውም ዓይነት ስርዓት የተፈጸመ ጋብቻ በሕግ እኩል ውጤት አለው፡፡

አንቀጽ 59. የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈጸም

ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈጸሙ ወይም ተፈጽሟል ብሎ መገመት አስፈላጊ አይደለም፡፡

አንቀጽ 60. የጋብቻ ውል

1. ተጋቢዎች ትዳራቸውንና ሃብታቸውን በተመለከተ ከመጋባታቸው በፊት ወይም ጋብቻቸው በሚፈጽሙበት ዕለት በውል ሊስማሙ ይችላሉ፣
2. እንዲሁም በዚህ ውል ውስጥ በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት አንዱ ላንዱ ማድረግ ያለበትን ግዴታና ማግኘት ያለበትን መብት ሊገልጹ ይችላሉ፡፡

www.abyssinialaw.com



3. ኣብ መንጎኦም ፍልልይ ከይግበር ዝወፁ ሕጊታት ዝፀንዑ'ዮም፡፡

**ዓንቀፅ 61. ክስበት ምስኣን**

1. ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ ዝገብሮ ውዕል ሓዳር ባዕሉ እንተዘይፈፂሙዎን ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እንተዘይኣፅዲቑዎን ውፅኢት ኣይህልዎን፡
2. ብሕጊ ዝተኸልከለ ሰብ ውዕሊ ሓዳር ንምውዕንል ብዝተመልከተ ክእለት ከምዘለዎ ይቑፀር፡፡

**ዓንቀፅ 62. ስርዓት ውዕሊ (ፎርም)**

ውዕሊ ሓዳር ብፅሑፍ እንተዘይኮይኑን ኣርባዕተ ምስክራት ክልተ ብወገን ሰብኣይ ክልተ ብወገን ሰበይቲ ዝፈረሙሉ እንተዘይኮይኑን ውፅኢት ኣይህልዎን፡፡

**ዓንቀፅ 63. ውዕሊ ሰነድ ዝቕመጠሉ ቦታ**

1. ሓደ ቅዳሕ ኣብ ሓዳር ውዕሊ ንምውዕዓል ወይ ንምምዝጋብ ስልጣን ኣብ ዘለዎ ኣካል ይቕመጥ፡
2. እቶም ሰብ ሓዳር ክርእይዎ እንትደልዩ ወይ ካሊእ ሰብ ንኽሪኦ እንትፈቕዱ ወይ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ዝፈቐደሎም ሰባት ነቲ ውዕሊ ፅሑፍ ምርኣይ መሰል ኣለዎም፡፡

**ዓንቀፅ 64. ሓዳር ውዕሊ ኣብ ምውዕዓሉ ዘለዎ ደረት**

1. ሓዳር ውዕሊ ኣብ ሳልሳይ ወገን ንዝኾነ ግቡእ ከስዕብ ወይ ኣዛዝነት ኣብ ዘለዎም ሕጊ ድንጋገታት ኩነታት ምቅዋም ከምፅእ ኣይኽእልን፡
2. ከምኡ'ውን ተማራዓውቲ ሓፈሻዊ ብዝኾነ ልምዲ ወይ ሃይማኖት ወይ ሕጊ ጥራሕ ብምጥቃስ ተሰማዕሚዕና ኢና ብምባል ዝገብሩዎ ሓዳር ውዕሊ ውፅኢት የብሉን፡፡

**ዓንቀፅ 65. ምምሕያሽ ሓዳር ውዕሊ**

1. ሓዳር ውዕሊ ንክመሓየሽ ሰብኣይን ሰበይትን ብዘቕርብዎ ሕቶ መሰረት ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ከፅድቐሎም ይኽእል፡



3. በመካከላቸው ልዩነት እንዳይደረግ የወጡ ሕጎች የጸኑ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 61. ችሎታ ማጣት**

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገው የጋብቻ ውል እርሱ ራሱ ካልፈጸመውና ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ካላጸደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡
2. በሕግ የተከለከለ ሰው የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 62. የውሉ ስርዓት (ፎርም)**

የጋብቻ ውል በጽሑፍ ካልሆነና አራት ምስክሮች ሁለት በባል ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 63. የውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ**

1. አንድ ቅጂ የጋብቻ ውል ለማዋዋል ወይም ለመመዝገብ ስልጣን ባለው አካል ይቀመጣል፡፡
2. ተጋቢዎች ለማየት ሲፈልጉ ወይም ሌላ ሰው እንዲያየው ሲፈቅዱ ወይም በማሕበራዊ ፍርድ ቤት የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ጽሑፍ ለማየት መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ 64. የጋብቻ ውል ስመዋዋል ስላለው ወሰን**

1. የጋብቻ ውል በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ማንኛውም ግዴታ የሚያስከትል ወይም አዛዥነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ላይ የመቃወም ሁኔታን ማምጣት አይችልም ፤
2. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ልምድን ወይም ሃይማኖትን ወይም ሕግን በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት የለውም፡፡

**አንቀጽ 65. የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል**

1. የጋብቻ ውል እንዲሻሻል ባልና ሚስት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊያጸድቅላቸው ይችላል፤

www.abyssinialaw.com



2. ጥቕሚ ስድራ ክሕሉ ኣድላይ ኣብ ዝኾነሉ እዋን ካብ ሰብ ሓዳር ብሓዲኦም ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሕቶ እንትቐርብ ሓዳር ውዕሊ ክማሓየሽ ይክእል፡፡
3. እቲ ዝተማሓየሸ ሓዳር ውዕሊ ምዃኑ ዘመልክት ፅሑፍ ኣብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ወይ ኣብ ሓዳር ውዕል ዘወዓዕል ወይ ክምዝግብ ስልጣን ዝተውሃበ ኣካል ይቕመጥ፡፡

## ዓንቀፅ 66. ኣብ መንጎ ሰብኣይን ሰበይቲን ዝግበር ውዕሊ

ሰብኣይን ሰበይትን ብሓዳር ክነብሩ እንተለው ኣብ መንጎኦም ዝግበር ውዕሊ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እንተዘይኣፅዲቕዎ ብሕጊ ተቐባልነት የብሉን፡፡

## ዓንቀፅ 67. ሕጋዊ ተፈፃምነት

ሓዳር ውዕሊ ዘየሎ እንተኾይኑ ወይ ሓዳር ውዕሊ ስምምዕ ወይ ኣብ መንጎ ሰብኣይን ሰበይትን ዝተገበረ ውዕሊ ከይፀደቐ ዝተረፈ እንተኾይኑ ካብዚ ቀፂሎም ብዝተመልከቱ ክፍሊ ክልተን ሰለስተን ድንጋጌታት መሰረት ይፍፀም፡፡

## ክፍሊ ክልተ
## ሓዳር ኣብ ልዕሊ ሰብ ሓዳር ውልቃዊ ርክብ ዘለዎ ውፅኢት

## ዓንቀፅ 68. መራሒ ቤተሰብ

ሰብኣይን ሰበይትን ሓዳሮም ዝምልከት ኩሉ ብሓባርን ብማዕረን የመሓድሩ፡፡

## ዓንቀፅ 69. ምክብባር፣ ምርድዳእን ምትሕግጋዝን

1. ሰብኣይን ሰበይትን ንንሕድሕዶም ምክብባር፡ ምርድዳእን ምትሕግጋዝን ኣለዎም፡
2. ኣብ ውሽጢ ሓዳር ውዕሊ ነዚ ዝፃባእ ስምምዕ ክገብሩ ኣይኽእሉን፡፡

## ዓንቀፅ 70. ግቡእ ምትእምማን

ሰብኣይ ንሰበይቱ፥ ሰበይቲ ንሰብኣያ ተኣማኒ ናይ ምዃን ግቡእ ኣለዎም፡፡



2. የቤተሰብን ጥቅም ለመጠበቅ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከተጋቢዎች በአንደኛው ጥያቄው ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የጋብቻው ውል ሊሻሻል ይችላል፡
3. የጋብቻው ውል የተሻሻለ መሆኑን የሚያመለክት ጽሑፍ በማሕበራዊ ፍርድ ቤት ወይም የጋብቻ ውል ለማዋዋል ወይም ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው አካል ይቀመጣል፡፡

## አንቀጽ 66. በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ውል

ባልና ሚስት በጋብቻ አብረው ሲኖሩ በመካከላቸው የሚደረግ ውል ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ካላጸደቀው በስተቀር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 67. የሕግ ተፈጻሚነት

ጋብቻ ውል የሌለ እንደሆነ ወይም የጋብቻ ውል ስምምነት ወይም በባልና ሚስት መካከል የተደረገው ውል ሳይጸድቅ የቀረ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት በክፍል ሁለትና ሶስት ድንጋጌዎች መሰረት ይፈጸማል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ጋብቻ በተጋብዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ 68. የቤተሰብ መሪ

ባልና ሚስት ትዳራቸውን በተመለከተ ሁሉ በጋራና በእኩልነት ያስተዳድራሉ፡፡

## አንቀጽ 69. መከባበር ፣ መረዳዳትና መተጋገዝ

1. ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር፡ መረዳዳትና መተጋገዝ አለባቸው፡
2. በጋብቻው ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም፡

## አንቀጽ 70 የመተማመን ግዴታ

ባል ለሚስቱ፥ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡

www.abyssinialaw.com





## ዓንቀፅ 71. ብዛዕባ ምምሃሮም ስድራ (1) ሓፈሻዊ ኩነታት

1. ሰብኣይን ሰበይትን ደሕንነትን ረብሓን ስድረኦም ማእኸል ብምግባር ብዛዕባ ስነ-ምግባርን ተፈጥራዊ ዕብየትን ደቆም ንምርግጋፅ ከምኡ'ውን ንደቆም ብፅቡቕ ኩነታት ንምዕባይ ዓርሶም ዝኽእልሉ መንገዲ ብምትላም ክተሓበበሩን ብሓባር ኮይኖም ስድራ ክመርሑን ኣለዎም፡፡

## ዓንቀፅ 72. ካብ ሰብኣይን ሰበይቲን ሓዲኦም ክእለት እንተስእኑ/2/

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ክእለት እንተስኢኖም ወይ ኣብቲ ዝነበርሉ ቦታ ዘይርከቡ እንተኾይኖም ወይ ድማ ስድርኦም ብምግዳፍ ዝተፈረዶም እንተኾይኖም እቲ ሓደ በይኑ ነቲ ሓላፍነት ስድራ ምምሕዳርን ምምራሕን ኣጠቓሊሉ ይፍፅም፡
2. ካብ ክልቲኦም ሓደ ሓበራዊ ናብረኦም ብፍቓዱ ገዲፉ ዝኸደ እንተኾይኑ ወይ ካብቲ ዝነብረሉ ቦታ ብምርሓቁ ይኹን ብዝኾነ ካልእ ምኽንያት ሓሳቡ ንምግላፅ ኣብዘይኽእለሉ ኩነታት እንተርከብ በዚ ልዕል ኢሉ ዝተደንገገ መሰረት ይፍፀም ፡
3. ሰብኣይን ሰበይትን ኣብ ውሽጢ ሓዳር ውዕሎም ነዚ ዝፃባእ ስምምዕ ክገብሩ ኣይኽእሉን፡፡

## ዓንቀፅ 73. ቅድሚ ሓዳር ካብ ካሊእ ብዛዕባ ዝተወለዱ ቖልዑ

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ቅድሚ ሓዳር ካብ ካሊእ ዝወለድዎም ቆልዑ ኣታዓባብያ ብዝምልከት ብናይ ባዕሎም ሓሳብን መሪሕነትን ንምውሳን ሙሉእ መሰል ኣለዎም፡
2. ነዚ ስርዓት ዝፃባእ ዝኾነ ስምምዕነት ሕጋዊ ውፅኢት የብሉን ፡፡

## ዓንቀፅ 74 ብሓባር ምንባር

1. ሰብኣይን ሰበይቲን ብሓባር ክነብሩ ይግደዱ፡
2. ንጥዕነኦም ሓደገኛ ክሳብ ዘይኮነ ሰብኣይን ሰበይትን ካብ ሓዳር ዝሕሎ ስሩዕ ፆታዊ ርክብ ክፍፅሙ ኣለዎም፡
3. ነዚ ዝፃባእ ዝኾነ ስምምዕነት ሕጋዊ ውፅኢት የብሉን፡፡

## አንቀጽ 71. ስለቤተሰብ አመራር (1) ጠቅላላ

1. ባልና ሚስት በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ድህንነትና ጥቅም ማእከል በማድረግ /ለማስጠበቅ/ ስለልጆቻቸው ስነ-ምግባርና ተፈጥሮአዊ እድገትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ልጆቻቸው በጥሩ ሁኔታ ለማሳደግና ራሳቸው የሚችሉበትን መንገድ በመቀየስ መተባበርና በጋራ ሆነው ቤተሰብ ሠምራት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 72. ከባልና ሚስት አንደኛው ችሎታ ሲያጡ (2)

1. ከባልና ከሚስት አንደኛው ችሎታ ያጣ ወይም በሚኖርበት አከባቢ (ቦታ) የማይገኝ እንደሆነ ወይም ቤተሰቡን በመተው የተፈረደበት እንደሆነ ቤተሰብን የማስተዳደርና የመምራት ሓላፊነትን አንደኛው ብቻውን አጠቃልሎ ይፈጽማል፡
2. ከሁለቱ አንደኛው የጋራ ኑሮአቸውን በፈቃዱ ጥሎ የሄደ እንዳሆነ ወይም ከሚኖርበት ቦታ በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ሃሳቡን መግለጽ በማይችልበት ሁኔታ ሲገኝ ከፍ ሲል በተደነገገው መሰረት ይፈጸማል፡
3. ባልና ሚስት በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 73. ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች

1. ከባልና ሚስት አንዱ ከጋብቻ በፊት ከሌላ የወለዱዋቸውን ልጆች አስተዳደግ በሚመለከት በራሳቸው ሃሳብና መሪነት የመወሰን ሙሉ መብት አላቸው፡
2. ይህንን ስርዓት የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 74 አብሮ መኖር

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ፡
2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው፡
3. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ሕጋዊ ውጤት የለውም፡፡

www.abyssinialaw.com





ዓንቀፅ 75. ብዛዕባ ምውሳን መንበሪ ቦታ

1. መንበሪ ቦታ ሰብኣይን ሰበይትን ብስምምዕነት ክልቲኦም ይውሰን፡

2. ኣብ ስምምዕ ክበፅሑ እንተዘይክኢሎም ብክልቲኦም ወይ ብሓዲኦም ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥርዓን ክቐርብ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 76. ብስምምዕነት ተፈላሊኻ ምንባር

1. ኣብዚ ሕጊ ዓንቀፅ 74 ንኡስ ዓንቀፅ (1) ዝተጠቐሰ ከምዘሎ ኮይኑ ሰብኣይን ሰበይትን ንዝተወሰነ ወይ ንዘይተወሰነ እዋን ተፈላልዮም ንምንባር ክስማዕምዑ ይኽእሉ'ዮም፡

2. ብዛዕባ'ዚ ዝተደንገገ ስምምዕ ምልዋጡ ዘይግቡእ እንተዘይኮይኑ ካብ ክልቲኦም ሰብ ሓዳር ሓዲኡ ሓሳቡ ክሰርዞ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 77. ሰብኣይን ሰበይትን ብዛዕባ ምምራፅ ሙያዊ ስራሕ

ሰብኣይን ሰበይትን ሕድ ሕዱም ብዝመረፅዎ ሞያ ስራሕ ክሰርሑ ይኽእሉ፡፡

ክፍሊ ሰለስተ

ሓዳር ኣብ ልዕሊ ንብረት ዘለዎ ውፅኢት

ዓንቀፅ 78 ውልቀ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን (1) ብዘይዕድጊት ዝተረኸበ ሃፍቲ

ሰብኣይን ሰበይትን ክሳብ ዕለት መርዖኦም ዝነበረ ውልቀ ሃፍቲ ወይ ድሕሪ መርዖኦም ብውርሲ ወይ ብውህብቶ ዝረኸብዎ ሃፍቲ ንነብሲ ወከፎም ውልቀ ሃፍቶም ኮይኑ ይነብር፡፡

ዓንቀፅ 79. ብዕድጊት ዝተረኸበ ሃፍቲ (2)

1. ምስተመራዓው ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓደ ብገንዘቡ ዝገዝኦ ሃፍቲ ውልቀ ሃብቲ እዩ፡፡ እዚ ዝኾውን ድማ እቲ ሃፍቲ ዝተረኸበ ብናይ ውልቀ ሃፍቲ ገንዘብ ዝገዝኦ ክኾውን እንከሎ ወይ ብናይ ውልቀ ገንዘብ ለውጢ ዝረኸቦ ሃፍቲ ክኾውን እንከሎ እዩ ፡፡

2. በዚ ዓይነት ዝተገዝአ ወይ ዝተረኸበ ሃፍቲ ካብ ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ሓዲኦም ናይ ውልቀይ ይኹነለይ ኢሉ ሕቶ ብዘቕረቦ መሰረት ብምግባር ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እንተዘይኣፅዲቕዎ ተፈፃምነት የብሉን፡፡

አንቀጽ 75. የመኖሪያ ስፍራን ስለመወሰን

1. ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ቦታ በሁለቱ ስምምነት ይወሰናል፤

2. ስምምነት ላይ ሊደርሱ ካልቻሉ በሁለቱም ወይም በአንደኛው ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 76. በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 74 ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባልና ሚስት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር ሊስማሙ ይችላሉ፤

2. ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መለወጡ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው እስቦ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

አንቀጽ 77. የባልና ሚስት የሙያ ስራ ስለመምረጥ

ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው በመረጡት የሙያ ስራ መስራት ይችላሉ፡፡

ክፍል ሶስት

ጋብቻ በንብረት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አንቀጽ 78. የባልና ሚስት የግል ሃብት (1) ያለግብይት የተገኙ ሀብቶች

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ የነበረ የግል ሀብት ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ሃብቶች የግል ሃብቶቻቸው ሆነው ይኖራሉ፡፡

አንቀጽ 79. በግብይት የተገኘ ሀብት(2)

1. ከተጋቡ በኃላ ከባልና ሚስት አንዱ በገንዘቡ የገዛው ሃብት የግል ሃብት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ሃብቱ የተገኘው በግል ገንዘቡ የገዛው ሲሆን ወይም የግል ገንዘቡ በሆነው ነገር ልዋጭ ያገኘው ሀብት የሆነ እንደሆነ ነው፤

2. በዚህ ዓይነት የተገዛ ወይም የተገኘ ሀብት የግል ይሁንልኝ ብሎ ከባልና ሚስት አንደኛው ወገን ባቀረበው ጥያቄ መሰረት በማድረግ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ካላጸደቀው በስተቀር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

www.abyssinialaw.com



ዓንቀፅ 80. ውፅቂ ሃፍቲ ብዛዕባ ምምሕዳር

(1) መትከል

1. ሕድ ሕድ በዓል ሓዳር ውልቂ ሃፍቲ ምምሕዳርን ኣታዊኡ ምቕባልን ይኽእል'ዩ፡
1. ሕድ ሕድ በዓል ሓዳር ካብ ውልቂ ሃፍቲ ዝተረኽበ ኣታዊ ባዕሉ ክእገዝ ነፃነት ኣለዎ፡፡

ዓንቀፅ 81. ምምሕዳር ውፅቂ ሃፍቲ ብሓዳር ውዕሊ ብዛዕባ ምውሳን (2)

1. ካብ ሰብኣን ሰበይትን ሓዲኦም ናይቲ ሓደ በዓል ሓዳሩ /ሓዳራ ውልቂ ሃፍቲ ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ከማሓደርሉን ከምኣድላነይቲ ክእገዝን ኣብ ሓዳር ውዕሎም ክውሰኑን ይኽእሉ፡
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) ብዝተደንገገ ውልቂ ሃፍቲ ከማሓድር ስልጣን ዝተውሃቦ በዓል ሓዳር ብዛዕባ እቲ ውልቂ ሃብቲ ምምሕዳር ዝምልከት በቲ በዓል ሓዳሩ /ሓዳራ እንትሕተት ዓመታዊ መግለፂ ሒሳብ ከቕርብ ግቡእ ኣለዎ፡፡

ዓንቀፅ 82./3/ ስልጣን ውክልና

ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ውልቂ ሃፍቲ ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ከማሓድረሉ ንበዓል ሓዳሩ ውክልና ምሃብ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 83. ሓበራዊ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን

1. ሰብኣይን ሰበይትን መሃያኦም ወይ ብውልቀ ወይ ብሓባር ፃዕሮም ክምኡ'ውን ካብ ሓባር ወይ ካብ ውልቀ ሃፍቶም ዝረኽቡዎም እቶታት ኩሎም ሓባራዊ ሃፍቶም'ዮም፤
2. ሰብኣይን ሰበይትን ምስተማራዓዉ ብገንዘብ ዝገዝእዎ ሃፍቲ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ናይ ሓዲኦም ውልቀ ሃፍቲ'ዩ ኢሉ ዘይወሰኖ ኩሉ ሓበራዊ ሃፍቶም'ዩ፡፡

ዓንቀፅ 84. ሕጋዊ ግምት

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ውልቀ ሃፍቲ ምዃኑ ከረድእ እንተዘይክኢሉ ዝኾነ ሃፍቲ ዋላ ብሽም እቲ ሓደ በዓል ሓዳሩ ዝተመዝገበ እንተኾነ ሓበራዊ ሃፍቲ ከምዝኾነ ይቑፀር፡



አንቀጽ 80. የግል ሀብትን ስለማስተዳደር

(1) መሰረቱ

1. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም መቀበል ይችላል፡
2. እያንዳንዱ ተጋቢ ከግል ሃብቱ የተገኘ ገቢ ራሱ ሊያዝበት ነፃነት አለው፡፡

አንቀጽ 81. የግል ሀብት ስለተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን (2)

1. ከባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(1) በተደነገገው አኳኋን የግል ሀብት እንዲያስተዳድር ስልጣን የተሰጠው ተጋቢ ስለየግል ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት ፡፡

አንቀጽ 82. የውክልና ስልጣን (3)

ከባልና ሚስት አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል ፡፡

አንቀጽ 83. የባልና የሚስት የጋራ ሀብት

1. ባልና ሚስት ደመወዛቸው ወይም በግል ጥረታቸው ወይም በጋራ ጥረታቸው እንዲሁም ከጋራ ወይም በግል ሀብታቸው ያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ናቸው፡
2. ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በገንዘብ የገዙት ሀብት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የአንዱ የግል ሀብት ነው ብሎ ያልወሰነው ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ነው፡፡

አንቀጽ 84. የሕግ ግምት

1. ከባልና ሚስት አንደኛው የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ሀብት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳ የጋራ ሃብት እንደሆነ ይቆጠራል፡

www.abyssinialaw.com



2. ውልቀ ሃፍቲ ምዃኑ ካልኦት ሳልሳይ ወገናት ክፈልጥዎ ወይ ክፈልጥዎ ዝግባእ እንተዘይኮይኑ ሰብኣይን ሰበይትን ወይ ካብ ክልቲኦም ሓዲኦ እዚ ንብረት ናይ ውልቀ እዩ ብምባል ኣብ ልዕሊ ሳልሳይ ወገን መቃወሚ ጌሮም ክቐርብዎ ኣይኽእሉን፡፡

ዓንቀፅ 85. ብዛዕባ ኣታዊ ሰብኣይን ሰበይትን /1/ ስርዓት ኣማሓዳድራ ኣታዊ

1. ሰብኣይን ሰበይትን ሕድ ሕዶም ዝረኽብዎም ኣታዊ ባዕሎም ይቕበሉ፣
2. ሰብኣይን ሰበይትን በቢ ውልቆም ዝረኽብዎ ኣታዊ ብውልቀ ወይ ብሓባር ባንኪ ሒሳብ ብምኽፋት ምቕማጥ ይኽእሉ፣
3. ካብ ክልቲኦም ብሓዲኦም ሕቶ እንትቐርብ ካብ መሃይን ካብ ንብረትን ዝተረኽበ መጠን ኣታዊ ክገልፅ ግቡእ ኣለዎ፡፡

ዓንቀፅ 86. ፍሉይ ኩነታት (2)

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ዝግበኦ ኣታዊን መሃይን እቲ ሓደ ንኽቕበለሉ ሓላፍነት ክህብ ሙሉእ ነፃነት ኣለዎ፣
2. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ብሓዲኦም ሕቶ መቕረበይነት ናይቲ ሓደ እቶት እቲ ሓደ ክቕበለሉን ንምቕባሉ ቅብሊት ክህብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ክውስን ይኽእል'ዩ፡፡
3. ብኻሊእ ሕጊ ብፍሉይ እንተዘይተደንጊጉ ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ናይ ሓዲኦም ኣታዊ ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ንኽእገድ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ክእዝዝ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 87. ብዛዕባ ምምሕዳር ሓባራዊ ሃፍቲ

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ናይ ሓባር ሃፍቶም ብሙሉእ ወይ ብክፋል ከማሓድር ግልፂ ስምምዕ እንድሕር ዘይሃሊዩ ሰብኣይን ሰበይትን ሓባራዊ ሃፍቶም ብሓባር የማሓድሩ፣

2. ኣብዚ ኣንቀፅ ኣብ ንኡስ ኣንቀፅ 1 ዝተጠቐሰ ከምዘሎ ኾይኑ ኣብ ኣንቀፅ 72 ዘለዉ ድንጋገታት'ውን ዝተሓለዉ'ዮም፣



2. የግል ሀብት መሆኑን ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይኸው ሀብት የግል ነው በማለት በሶስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም፡፡

አንቀጽ 85. ስለባልና ሚስት ገቢ(1) መደበኛ የገቢ አስተዳደር

1. ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ፣
2. ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ፣
3. ከሁለቱ በአንዳኛው ጥያቄ ሲቀርብ ከደመወዝና ከንብረት የተገኘውን የገቢ መጠን የመግለጽ ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 86. ልዩ ሁኔታ(2)

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የሚገባውን ገቢ እና ደመወዙን ለአንደኛው እንዲቀበልለት ሀላፊነት ለመስጠት ሙሉ ነፃነት አለው፣
2. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጥያቄ አቅራቢነት የአንደኛው ገቢ ሌላኛው እንዲቀበልለት እና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል፣
3. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከባልና ከሚስት የአንደኛ ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲታገድ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊያዝ ይችላል፡፡

አንቀጽ 87. የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ፣

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ በአንቀጽ 72 ያሉት ድንጋጌዎችም የተጠበቁ ናቸው፣

www.abyssinialaw.com



3. ካብዚ ወፃኢ ብዘልዕልዎ ሕቶ መሰረት ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ናይ ሓባር ንብረቶም ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ንከማሓድርዎም ከም ኣድላይነቱ ነቲ ሰብኣይ ወይ ነታ ሰበይቲ ክፈቕደሎም ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 88. ናይ ምፍላጥ ግቡእ

ካብቶም ሰብሓዳር ሓዲኦም በይኑ ሓበራዊ ንብረት ኣብ ዘማሓድረሉ እዋን ኣማሓዳድራ እቲ ሃፍቲ ብዝምልከት ንበዓል ሓዳሩ መረዳእታ ናይ ምሃብ ግቡእ ኣለዎ፡፡

ዓንቀፅ 89.(1) ስምምዕ ክፅቲሶም ሰብ ሓዳር ኣድላይ ብዛዕባ ምዃኑ

ብኻሊእ ሕጊ ብዝተፈለየ መልክዑ ክሳ ዘይተደንገገ ቀፂሎም ኣብ ዘለዉ ዋኒናት ስምምዕ ሰብኣይን ሰበይትን ኣድላይ እዩ፡፡

ሀ. ዝኾነ ዘይንቀሳቐስ ሓባራዊ ንብረት ንምሻጥ ንምልዋጥ፣ ንምክራይ፣ ብትሕጃ ወይ ብውሕስና ንምሃብ ወይ ብኻሊእ መልክዑ ኣብ ርእሲ'ዚ ንብረት ካልኦት ሰባት መሰል ንኽረክቡ ንምግባር፣

ለ. ዋጋኦም ካብ ብር 500 / ሓሙሽተ ሚኢቲ ብር / ንላዕሊ ዝኾኑ ዝንቀሳቐሱ ናይ ሓባር ንብረታት ወይ ናይ ገንዘብ ሰነዳት ንምሻጥ፣ ንምልዋጥ፣ ብመትሓጃ ወይ ብውሕስና ንምሃብ ወይ ብኻሊእ መልክዕ ንምትሕልላፍ፣

ሐ. ካብ ብር 100 / ሓደ ሚኢቲ ብር / ንላዕሊ ዋጋ ዘለዎ ናይ ሓባር ንብረት ወይ ገንዘብ ንኻሊእ ሰብ ብውህብቶ ንምትሕልላፍ፣

መ. ካብ ብር 500 / ሓሙሽተ ሚኢቲ ብር / ንላዕሊ ንምልቃሕ ወይ ብልቓሕ ንምሃብ ወይ ንኻሊእ ሰብ ዋሕስ ንምዃን፡፡

ዓንቀፅ 90.(2) ስምምዕ ዘይምህላው ዘስዕቦ ውፅኢት

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ካብዚ ንላዕሊ ብዝተጠቐሰ ድንጋጌ ብዘይምኽባር ግቡእ ዘእትው ውዕሊ ኣትዮም እንድሕር ተረኺቦም እቲ ሓደ በዓል ሓዳር ብመሰረት ንማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ብዘቕርቦ ሕቶ እቲ ግቡእ ክፈርስ ይኽእል'ዩ፡፡



3. ከዚህ ውጪ በሚያነሱት ጥያቄ መሰረት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የጋራ ሀብታቸው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድሯቸው እንዳአስፈላጊነቱ ለባል ወይም ለሚስት ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡

አንቀጽ 88. የማስታወቅ ግዴታ

ከተጋቢዎች አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

አንቀጽ 89.(1) የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው፡፡

ሀ. የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸው ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፣

ለ. ዋጋቸው ከ500 ብር /አምስት መቶ ብር/ በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ የጋራ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሰነዶችን፣ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ፣

ሐ. ከ100 ብር /አንድ መቶ ብር/ በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ፣

መ. ከ500 ብር (አምስት መቶ ብር) በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን፡፡

አንቀጽ 90.(2) ስምምነት ስለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል፣

www.abyssinialaw.com



2. ግቡእ ክፈርስ ዝቐርብ ሕቶ እቲ ሓታቲ ወገን ግቡእ ዝተኣተወ ምዃኑ ካብ ዝፈለጠሉ ዕለት ጀሚሩ ድሕሪ ሽዱሽተ ወርሒ ወይ ብኻሊእ መልክዕ ግቡእ ካብ ዝተኣተወሉ ድሕሪ ክልተ ዓመት ክቐርብ ኣይኽእልን፡፡

## ዓንቀፅ 91. ዕዳ ሰብኣይን ሰበይትን

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ዝሀልዎም ውልቀ ዕዳ ካብ ውልቀ ሃፍቶም ተቐኒሱ ነቲ ዕዳ መኽፈሊ ይኸውን፡፡ እቲ ዘለዎም ውልቀ ሃፍቲ ነቲ ዕዳ መኽፈሊ እኹል እንተዘይኮይኑ እቲ ዕዳ ዘለዎ በዓል ሓዳር ካብ ሓባር ንብረት ዝሀልዎ ክፋል ተቐኒሱ ነቲ ዕዳ መኽፈሊ ይኸውን፡
2. ዝመፀ ዕዳ ንሓዳሮም ጥቕሚ እንተደኣ ኮይኑ ግና ከም ሓባር ዕዳ ተቆፂሩ ካብ ሓባር ሃፍቶም፣ እቲ ሓባርዊ ሃፍቶም ነቲ ዕዳ ንምኽፋል እኹል ኣብ ዘይኾነሉ እዋን ካብ ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ውልቀ ሃብቲ ይኽፈል፡፡

## ዓንቀፅ 92. ንሓዳር ጥቕሚ ከምዝወዓለ ዝቑፀር ዕዳ

ንሓዳር ጥቕሚ ከምዝወዓለ ዝቑፀር ዕዳ፣

ሀ. ንሰብኣይን ሰበይትን ከምኡ'ውን ንደቆም ዕለታዊ መነባብሮ ኣድለይቲ ዝኾኑ ነገራት ንምምላእ ዝተኣተዉ ዕዳታት፣

ለ. ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ቀለብ ንምቕራብ ዘለዎም ግቡእ ንምፍፃም ዝተገበሩ ወፃኢታት፣

ሐ. ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦምን ወይ ብመመልከታይነት ዕዳ ሓታቲ እቲ ዝመፀ ዕዳ ንጥቕሚ ሓዳር ከምዝኾነ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ፈሊጡዎ ዝተቐበሎ ካሊእ ዕዳ፡፡

## ዓንቀፅ 93. ሰብኣይን ሰበይቲን ንሓዳሮም ዘድሊ መዓልቲ ብዝምልከት ዝገብርዎ ምትሕግጋዝ

ሰብኣይን ሰበይትን ንሓዳሮም ዝገብርዎ ወፃኢ ብመጠን ክእለቶምን ዓቕሞምን እናተሓጋገዙ ክኸውን ኣለዎ፡፡



2. ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 91. የባልና ሚስት ዕዳ

1. ከባል ወይም ከሚስት በአንደኛው የሚኖራቸው የግል ዕዳ ከግል ሀብታቸው ተቀንሶ ዕዳውን መክፈያ ይሆናል፡፡ ያለውን የግል ሀብት ዕዳውን ለመክፈል በቂ ካልሆነ ዕዳ ያለበት ተጋቢ ከጋራ ንብረቱ የሚኖረው ድርሻ ተቀንሶ ለዕዳው መክፈያ ይሆናል፣
2. ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ እንደጋራ ዕዳቸው ተቆጥሮ ከጋራ ሀብታቸው፣ የጋራ ሀብታቸው ዕዳውን ለመክፈል በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል፡፡

## አንቀጽ 92. ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ዕዳ

ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ዕዳ፡-

ሀ. ለባልና ሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የተገቡ ዕዳዎች፣

ለ. ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተዳረጉ ወጪዎች፣

ሐ. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት አውቆት የተቀበለው ሌላ ዕዳ፡፡

## አንቀጽ 93. ባልና ሚስት ለትዳራቸው የሚያስፈልግ ወጪ በሚመለከት የሚያደርጉት መተጋገዝ

ባልና ሚስት ለትዳራቸው የሚያደርጉትን የወጪ መጠን እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው እየተጋገዙ መሆን አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com





## ምዕራፍ ሓሙሽተ

## ምፍራስ ሓዳር

**ዓንቀፅ 94. ብዝተፈላለዩ ስርዓታት ዝተፈፀሙ ሓዳራት ክፈርሱ እንተለዉ ማዕረ ብዛዕባ ምዃኖም**

1. ብዝኾነ ይኹን ዓይነት ስርዓት ዝተፈፀመ ሓዳር ክፈርስ እንተሎ ዘስዕቦ ውፅኢት ማዕረ እዩ፣
2. እቲ ሓዳር ዝተፈፀመ ብዝኾነ ኣፈፃፅማ ስርዓት ሓዳር ዋላ እኳ እንተኾነ ናይቲ ሓዳር ምፍራስ ብዝተመልከተ ነገኾነ ኣፈላላይ ኣይግበረሉን፡፡

## ክፍሊ ሓደ

## ሓዳር ዝፈርሰሉ ምኽንያታት

**ዓንቀፅ 95. ዝተፈላለዩ ምኽንያታት**

ሓዳር ዝፈርስ በዞም ዝስዕቡ ምኽንያታት እዩ፡፡

1. ካብቶም ሰብ ሓዳር ሓዲኦም ክመውት እንተሎ፣ ወይ ስልጣን ብዘለዎ ቤት ፍርዲ ካብ ሰብ ሓዳር ሓዲኦም ብምጥፍኡ ውሳነ እንትህብ ፣ ወይ
2. ብምኽንያት ሓዳር ንምፍፃም ክማልኡ ካብዘለዎም ኩነታት ሓዲኦም ብምጥሓሱ ብመሰረት ሕጊ ሓዳር ክፈርስ እንትውሰን፣ ወይ
3. ውሳነ ፍትሕ እንትውሃብ እዩ፡፡

**ዓንቀፅ 96. ፍትሕ መሰል ብዛዕባ ምዃኑ**

ሰብኣይን ሰበይትን ብሓዳር ንምንባር ኣብ ዘይንኽእለሉ በፂሕና ኢና ብምባል ኣብ ዝኾነ እዋን ሕቶ ፍትሕ እንተቕሪቦም ምፍታሕ መሰሎም'ዩ፡፡

**ዓንቀፅ 97. ብስምምዕ ዝግበር ፍትሕ**

1. ሰብኣይን ሰበይትን ንምፍታሕ ዝገብርዎ ስምምዕ ብሕጋዊ መንገዲ እንተዘይተፈፂሙ ኣይፍቀድን፣
2. ኣብዚ ሕጊ ካብ ዝተመልከቱ ድንጋገታት ወፃኢ ብዝኾነ ኣፈፃፅማ ፍትሕ ንምውሳን ኣይከኣልን፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለጋብቻ መፍረስ

**አንቀጽ 94. በተለያዩ የጋብቻ ስርዓት የተፈጸሙ ጋብቻዎች ሲፈርሱ እኩል ስለመሆናቸው**

1. በማናቸውም ዓይነት ስርዓት የተፈጸመ ጋብቻ ሲፈርስ የሚያስከትለው ውጤት እኩል ነው፣
2. ጋብቻው የተፈጸመው በማናቸውም የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ቢሆንም፣ የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት አይደረግበትም፡፡

## ክፍል አንድ

## ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች

**አንቀጽ 95. የተለያዩ ምክንያቶች**

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፣

1. ከተጋቢዎች አንዱ ሲሞት ወይም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ከተጋቢዎቹ አንዱ በመጥፋቱ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ወይም
2. ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በህግ መሰረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ ወይም
3. የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ፡፡

**አንቀጽ 96. ፍቺ መብት ስለመሆኑ**

ባልና ሚስት በጋብቻ አብረን ለመኖር በማንችልበት ደረጃ ደርሰናል በማለት በማንኛውም ጊዜ የፍቺ ጥያቄ ካቀረቡ መፋታት መብታቸው ነው፡፡

**አንቀጽ 97. በስምምነት የሚደረግ ፍቺ**

1. ባልና ሚስት ለመፋታት የሚያደርጉት ስምምነት በሕጋዊ መንገድ ካልተፈጸመ አይፈቀድም፣
2. በዚህ ሕግ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውጪ በማንኛውም አፈጻጸም ፍቺን መወሰን አይቻለም፡፡

www.abyssinialaw.com





ዓንቀፅ 98. ንምፍታሕ ብዛዕባ ዝቐርብ ሕቶ

1. ካብ ሰብኣይን ሰበይቲን ሓዲኦም ወይ ክልቲኦም ብሓንሳብ ኮይኖም ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሕቶ ፍትሕ ከቕርቡ ይኽእሉ፣
2. ካብዚ ወፃኢ ሕቶ ፍትሕ ብኻሊእ ሰብ ክቐርብ ኣይኽእልን፣
3. ቅድሚ ናይ ፍትሕ ውሳነ ምውሃቡ ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም እንተሞይቶም እቲ ንፍትሕ ተጀሚሩ ዝነበረ ከይዲ ይቋረፅ፡፡

ዓንቀፅ 99. ንግዚኡ ዝውሃቡ ውሳነታት

1. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሕቶ ፍትሕ ምስ ቀረበሉ ሽዑ ንሽዑ ሰብኣይን ሰበይትን ደቆምን ዝነባበርሉ፣ መማሓደሪ ወይ ኣታሓሳልዋ ንብረት ሰብኣይን ሰበይትን ዝምልከት ዋኒን ክሕዝ ዝግበኦ ስርዓት ኣተሓሳልዋ ከምኩነታቱ ኣብቲ ዋኒን ዝፀንዕ ንግዚኡ ውሳነ ይህብ፣
2. መንበሪ ቦታ ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ወይ ክልቲኦም ክኸድዎ ዘይግባእ ቦታ ፈልዩ ንውሱን እዋን ክውስኑ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 100. መሰል ምልዋጥ ወይ ምምሕያሽ

ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ንግዚኡ ዝሃቦ ውሳነ ካብቶም ሰብ ሓዳር ብሓዲኦም ብዝቕርብዎ ጥርዓን ኣብ ዝኾነ እዋን ክልውጦ ወይ ክግደፍ ክገብሮ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 101. ንምትዕራቕ ዝግበር ፈተነ

1. ሕቶ ፍትሕ ዝቐረበሉ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሰብኣይን ሰበይትን ብዝመረፅዎም ሽማግለታት ክዕረቑን ናይ ምፍታሕ ሓሳቦም ክገድፍዎን ዕድል ክህቦም ኣለዎ፣
2. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣብ መንጎ ሰብኣይን ሰበይትን ዘሎ ዘይምስምማዕ ንምዕራይ ዕቡቕ መሲሉ ዝተራእዮ ግዘ ገደብ ይውስነሎም፡፡

አንቀጽ 98. የፍቺ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለማህበራዊ ፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፣
2. ከዚህ ውጭ የፍቺ ጥያቄ በሌላ ሰው ሊቀርብ አይችልም፣
3. የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከባልና ሚስት አንዱ የሞቱ እንደሆነ ተጀምሮ የነበረው የፍቺ ሂደት ይቋረጣል፡፡

አንቀጽ 99. ለጊዜው የሚሰጡ ውሳኔዎች

1. ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የፍቺ ጥያቄ እንደቀረበለት ወዲያውኑ ባልና ሚስት እንዲሁም ልጆቻቸው የሚኖሩበትን መተዳደሪያ ወይም የባልንና ሚስት የንብረታቸው አጠባበቅ የሚመለከት ጉዳይና ሊይዝ የሚገባው ያጠባበቅ ስርዓት እንደየሁኔታው በጉዳዩ ላይ ለጊዜው የሚጸና ውሳኔ ይሰጣል፣
2. የባልየውን ወይም የሚስቲቱን መኖሪያ ቦታ ወይም ሁለቱም ሊሄዱበት የማይገባ ቦታ ለይቶ ለተወሰነ ጊዜ ሊገድብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 100. የመቀየር ወይም የማሻሻል መብት

ከተጋቢዎቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት አቤቱታ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ለጊዜው የሰጠው ውሳኔ በማንኛውም ጊዜ ሊለውጠው ወይም ሊያስቀረው ይችላል፡፡

አንቀጽ 101. ለማስታረቅ የሚደረግ ሙከራ

1. የፍቺ ጥያቄ የቀረበለት ማህበራዊ ፍርድ ቤት ባልና ሚስት በሽማግሌዎች እንዲታረቁና የመፍታት ሃሳባቸው እንዲተው ዕድል መስጠት አለበት፣
2. በባልና ሚስት መካከል ያለው ያለመስማማት ለማጣራት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ጥሩ መስሎ ከታየው የጊዜ ገደብ ይወሰንላቸዋል፡፡

www.abyssinialaw.com





**ዓንቀፅ 102. ብዛዕባ ኩነታት ፍትሕ ዝግበር ስምምዕነት**

1. ሰብኣይን ሰበይትን ሓሳባቶም ዘይልውጡ ምዃኖም ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እንተደኣ ተረዲኡ ፍትሖም ብስምምዕን ብምርድዳእን ንኽፈላለዩ ክፅዕር ኣለዎ፣
2. ከምዚ ዝመሰለ ሰምምዕ እንትርከብ እንተሎ በቲ ንምፍታሕ ዝገብርዎ ስምምዕ መሰረት ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ውሳነ ፍትሕ ይህብ፡፡

**ዓንቀፅ 103. ውሳነ ፍትሕን ውፅኢቱን ንምሃብ ዝግበር ግዘ ገደብ**

ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥርዓን ፍትሕ ካብ ዝቐረበሉ እዋን ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ ሽዱሽተ ወርሒ ውሳነ ፍትሕ ይህብ፡፡

**ዓንቀፅ 104. ኣብ ውሳነ ፍትሕ ዝፀሓፍ ቃል**

1. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ውሳነ ፍትሒ ዘስዕቦ ውፅኢት ኣብቲ ዝህቦ ብይን ክገልፅ ኣለዎ፣
2. ካብ ሓዳር ውሽጢ ዝተወለዱ ህፃናት ዝሕለዉሉን ዝዓብዩሉን ጉዳይ ብዝምልከት ከምኡ'ውን ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን ብዝምልከት መቐሎ ክፍፀም ይገብር፡፡

**ዓንቀፅ 105. ኣተሓሕዛ ህፃናት (1) መትከል**

1. ካብቶም ሰብሓዳር ዝተወለዱ ህፃናት ኣተሓላልዋን ኣታሓሕዛን ብዝምልከት ጉዳይ ዝተሓላለፈ ውሳነ ጥቕምን ፅቡቕ ናብራን ህፃናት ዝሕሉ ክኸውን ኣለዎ፣
2. ካብዚ ዝተፈለየ ውሳነ ንምሃብ ዘገድድ ምኽንያት እንተዘይኣጋጢሙ እቶም ህፃናት ሓሙሽተ ዓመት ክሳብ ዝመልኡ ምስ ኣዲኦም ክምዝኾኑ ይግበር፣
3. ድሕሪ ሓሙሽተ ዓመት ህፃናት ምስ ዝመርፅዎ ኣቦ ወይ ኣደ ክነብሩ ይኽእሉ እዮም፡፡

**106.(2) ውሳነ ዝመሓየሽሉ ኩነታት**.

ብዛዕባ ኣታሓላልዋን ኣታዓባብያን ህፃናት ዝተውሃበ ውሳነ ብኣደ ወይ ብኣቦ ወይ ንላዕሊ ብዝቐፀሩ ወለዲ ብዘቕርብዎ ጥርዓን መሰረት ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝኾነ እዋን ከማሓይሾ ይኽእል'ዩ፡፡

**አንቀጽ 102. ስለፍቺ ሁኔታዎች የሚደረግ ስምምነት**

1. ባልና ሚስት ሀሳባቸውን የማይለውጡ መሆናቸውን ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ከተረዳ ፍቺያቸውን በስምምነትና በመግባባት እንዲለያዩ መጣር አለበት፣
2. እንዲህ የመሰለ ስምምነት ሲገኝ ለመፍታት የሚያደርጉት ስምምነት መሰረት በማድረግ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 103. ስለፍቺና ውጤቱ ውሳኔ ለመስጠት የሚደረግ የጊዜ ገደብ**

ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የፍቺ አቤቱታ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 104. በፍቺ ውሳኔ ላይ የሚጻፈው ቃል**

1. ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ የሚያስከትለውን ውጤት በሚሰጠው ብይን ላይ መግለጽ አለበት፣
2. ከጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ህጻናት የሚጠበቁበትንና የአስተዳደጋቸው ጉዳይ በተመለከተ እንዲሁም የባልና ሚስት ንብረት በሚመለከት ክፍፍል እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 105. የህፃናት አጠባበቅ (1) መሰረቱ**

1. ከተጋቢዎቹ የተወለዱትን ህፃናት አጠባበቅና አያያዝን በሚመለከት ጉዳይ የተላለፈውን ውሳኔ የህጻናቱ ጥቅምና መልካም ኑሮ የሚጠብቅ መሆን አለበት፣
2. ከዚህ የተለየ ውሳኔ ለመስጠት አስገዳጅ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር ህፃናቱ ዕድሜቸው አምስት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ከእናታቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፣
3. ከአምስት ዓመት በኃላ ህፃናቱ ከመረጡት አባት ወይም እናት መኖር ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 106. ውሳኔው የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች**

ስለህፃናት አጠባበቅና አስተዳደግ የተሰጠውን ውሳኔ በእናት ወይም በአባት ወይም ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆች በሚያቀርቡት አቤቱታ መሰረት ማሕበራዊ ፍርድ ቤት በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com



## ክፍሊ ክልተ

## ብዛዕባ ምዕራይ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን

### ንኡስ ክፍሊ ሓደ

### ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ናይ ሓዲኦም ምሟት

**ዓንቀፅ 107. ናይ ምስምማዕ ነፃነት**

1. ካብ ሰብ ሓዳር ሓዲኡ እንተሞይቱ ጉዳይ መቐሎ ሃፍቶም ዝፃረ ብመሰረት ኣብ ሓዳር ውዕሎም ብዝተገበረ ስምምዕ ቃል ወይ ብመሰረት ኣብ መንጎ ሰብ ሓዳር ብዝተገበረ ስምምዕ እዩ፣
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ብዝተገለፀ ዓይነት ስምምዕ ዘየለ እንተኾይኑ ወይ እዚ ስምምዕ ብዝፀንዕ መንገዲ ከይተፈፀመ እንተተሪፉ ኣገባብ ክፍፍል ሃፍቲ ሰብ ሓዳር ዝፍፀም ብመሰረት ኣብዚ ክፍሊ ብዝተደንገገ ስርዓት እዩ፡፡

**ዓንቀፅ 108. ብዛዕባ ውልቀ ሃፍቲ መሊስካ ምውሳድ**

1. ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ውልቀ ሃፍቱ ምዃኑ ብምርዳእ ውልቀ ሃፍቱ ዝኾነ ንብረት ብዓይነቱ መሊሱ ናይ ምውሳድ መሰል ኣለዎ፣
2. ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ካብ ውልቀ ሃፍቱ ዝኾነ ንብረት ንኻሊእ ሰብ ዝተማሓለለፈ ምዃኑን ካብዚ መሸጣ ወይ ብክራይ ዝተረኽበ ገንዘብ ናብ ሓባራዊ ሃፍቶም ዝተሓወሰ ምዃኑ እንድሕር ኣረዲኡ ምስዚ ንብረት ተመጣጣኒ ዝኾኑ ገንዘብ ወይ ንብረት ካብ ሓባራዊ ሃፍቶም ብመጀመሪያ ኣልዒሉ ክወስድ መሰል ኣለዎ፣
3. ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ነናይ ውልቀ ሃፍቶም ዘልዕልሉ ኩነታት እንትህሉ ክልቲኦም ኣብ መወዳእታ ካብ ዝተረኸበ መጠን ሃፍቲ ከከም ኣስተዋፅኦኦም ንኽበፅሑም ዝኽእል መጠን ክልዕሉ መሰል ኣለዎም፣

**ዓንቀፅ 109. ብዛዕባ ካሕሳ**

ተፃባኢ ዝኾነ ስምምዕ ወይ መተኣማመኒ ምስትኽኻል ሒሳብ ዋላ'ኳ እንተሃለወ ብዝሰርሖ ስራሕን ንናይ ሓባር ንብረቶም ወይ ንናይ ሓዲኦም ውልቀ ሃፍቲ ብዝጎድኡ ተግባራት ምኽንያት ካብቶም ሰብ ሓዳር እቲ ሓደ ንቲ ሓደ ካሕሳ ክኽፍሎ ንምግባር ዝከኣል፣



## ክፍል ሁለት

## የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት

### ንኡስ ክፍል አንድ

### ከባልና ሚስት የአንዳቸው መሞት

**አንቀጽ 107. የመስማማት ነፃነት**

1. ከተጋቢዎቹ አንደኛው የሞተ እንደሆነ የሀብታቸው የክፍፍል ጉዳይ የሚጣራው በጋብቻ ውላቸው መሰረት በተደረገው የስምምነት ቃል ወይም በተጋቢዎቹ መካከል በተደረገው ስምምነት መሰረት ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ዓይነት ስምምነት የሌለ እንደሆነ ወይም ይህ ስምምነት በሚጸና መንገድ ሳይፈጸም የቀረ እንደሆነ የተጋቢዎቹ የሀብት ክፍፍል የሚፈጸመው በዚህ ክፍል በተደነገገው ስርዓት መሰረት ነው፡፡

**አንቀጽ 108. የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ**

1. ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሃብቱ የሆነውን ንብረት በዓይነት መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል፣
2. ባል ወይም ሚስት የግል ሀብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑንና ከዚህ ግብይት ወይም ኪራይ የተገኘው ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላለቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከዚህ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል፣
3. ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንዳየአስተዋጽኦዋቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 109. ስለካሳ**

ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ወይም የሂሳብ ማስተካከል መተማመኛ ቢኖርም እንኳ በሰራቸው ስራዎችና የጋራ ሀብቶችን ወይም ያንዳኛውን የግል ሀብት በጎዱት ስራዎች ምክንያት ከተጋቢዎቹ አንዱ ለአንደኛው ካሳ እንዲከፍል ለማድረግ የሚቻለው፣

www.abyssinialaw.com



1. ንቲ ተግባር ዝፈፀሞ ወገን እዚ ንምግባር ሓላፍነት ዘይነበሮ እንተኾይኑ፣
2. ኢታሓላልዋ ሃፍቲ ካብ ሕግኽ ኣማሓዳድራ ዝተበገሰ ተግባር እንተኾይኑ ወይ ኣብ ርእሲ ሃፍቲ ከሳሲ ናይ ምጭብርባር ተግባር ዝተፈፀመ እንተኾይኑ እዩ፣
3. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1ን 2ን ዝቐረበ ሕቶ ካሕሳ እቲ ተፈፂሙ ዝበሃል ተግባር ሓዳር ቅድሚ ምፍራሱ ቅድሚ ሓሙሽተ ዓመት እንተኾይኑ ተቐባልነት የብሉን፡፡

## ዓንቀፅ 110. ብዘይ ቅግባብ ብዛዕባ ምህፋታም

ኣብ መንጎ ሰብኣይን ሰበይትን ተዓባኢ ስምምዕነት እንተዘይሃልዩ ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ናይ ሓዲኦም ውልቀ ሃፍቲ ካብ ዝኾነ ንብረት ንቲ ካሊእ ውልቀ ሃፍቲ ወይ ካብ ሓባራዊ ሃፍቶም ብዘይኣግባብ ዝሃፍተመ ምኽኑ እንተኣረጋጊኡ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ግቡእ ካሕሳ ክኸፍሎ ክእዝዝ ይኽእል፡፡

## ዓንቀፅ 111. መሰል ዕዳ ሓተትቲ ብዛዕባ ምኽባር

ካብ ሰብኣይን ሰበይትን ሓዲኦም ወይ ክልቲኦም ብሓባር ብማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ዝተረጋገፀ ወይ ክልቲኦም ዘኣመንሉ ዕዳ ምህላዉ ዝተፈለጠ እንተኾይኑ እዚ ዕዳ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን ቅድሚ ምክፍፋሉ ተቐዲሙ ንበዓል ዕዳ ዝኽፈል ይኸውን፡፡

## ዓንቀፅ 112. ምምቓል ሓበራዊ ሃፍቲ

1. እዞም ልዕል ክብሉ ተጠቒሶም ዘለዉ ድንጋገታትን ኣብ ሓዳር ውዕሊ ወይ ሰብ ሓዳር ብዝፀንዕ ኩነታት ዝተፈራረምሎም ውዕላትን ዝተሓለዉ ኮይኖም፣

ሀ. መቐሎ ሓበራዊ ሃፍቲ ሰብ ሓዳር ዝፍፀም ማዕረ ብማዕረ ይኸውን፡፡

ለ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1(ሀ) ዝተፈፀመ ብዓይነት ማዕረ ንምክፍፋል ዘይኽእል እንተኾይኑ እቲ ኣፈላላይ ብገንዘብ ተሓሲቡ ክከሓሐስ ይግበር፣

ሐ. ሃፍቲ ክፍፍል ክግበር እንከሎ ንሕድ ሕድ ሰብ ሓዳር ብዝበለፀ ጠቓምነት ኣለዎ እዩ ተባሂሉ ዝተኣመነሉ ንብረት ብቐዳምነት ብዝረኽብሉ ኣገባብ ክግበር ኣለዎ፣



1. ስራውን የፈጸመው ወገን ይህንን ለማድረግ ሓላፊነት ያልነበረው እንደሆነ፣
2. የሀብት ጠባቂነቱ ተግባር በመጥፎ ዓይነት አስተዳደር የተደረገ እንደሆነ ወይም በከሳሹ ሀብት ላይ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ እንደሆነ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት ዓመት በፊት የሆነ እንደሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 110. ያለ አግባብ ስለመበልጸግ

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ከባልና ሚስት የአንደኛው የግል ሀብት ንብረት የሌላኛው የግል ሀብት ወይም የጋራ ሀብታቸው ያለ አግባብ መበልጸጉን ያስረዳ እንደሆነ ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 111. የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማክበር

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በማሕበራዊ ፍርድ ቤት የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ፣ ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ ለባለዕዳው የሚከፈል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 112. የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል

1. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች በጋብቻ ውል ወይም በተጋቢዎች በሚጸና አኳኃን የተፈራረሙበትን ውሎች እንደተጠበቁ ሆኖው፤

ሀ. የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ክፍፍል የሚፈጸመው በእኩል ይሆናል፣

ለ. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) የተፈጸመው በዓይነት እኩል ለመከፋፈል የማይቻል እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ ታስቦ እንዲካካስ ይደረጋል፣

ሐ. የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ተጋቢ በይበልጥ ጠቃሚነት አለው ተብሎ የታመንባቸው ንብረቶች በቅድሚያ በሚያገኙበት አግባብ መደረግ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com





## ንኡስ ክፍሊ ክልተ

## ኩነታት ፍትሕ

### ዓንቀፅ 113. ሓፈሻዊ ስርዓት

1. ካብዚ ቀፂሎም ኣብ ዝተመልከቱ ዓንቀፃት ዘለዉ ድንጋገታት ዝተሓለዉ ኮይኖም ሰብ ሓዳር ኣብ ዝፋትሕሉ እዋን ርክብ ሃፍቶም ዝፃረ ካብ ክልቲኦም ሓደ ክመውት እንተሎ ብዝግበር ስርዓት ምዕራይን መቐለን ንብረት ዓይነት ይኸውን፡፡
2. ኣብ ውሽጢ እዞም ዓንቀፃት ተመልኪቶም ዘለዉ ድንጋገታት ብሓዳር ውዕሊ ኮነ ቅድሚ ሓዳር ውዕሊ ምፍራሱ ሰብ ሓዳር ብዝገብርዎ ብኻልእ ዓይነት ስምምዕ ክምዝተርፍ ምግባር ኣይከኣልን፡፡

### ዓንቀፅ 114. ኣብ ሓዳር ዝቐረበ ውህብትን ጥቕምን

1. ብምኽንያት ሓዳር ካብ ዝኾነ ይኹን ነቶም ሰብ ሓዳር ዝውሃብ ውህብቶን ጥቕምን እቲ ሓዳር ፀኒዑ ኣብ ዘለሉ እዋን ኮነ ድሕሪ ምፍራስ እቲ ሓዳር ንውሃብቲ ወይ ንውሃብቲ ወረስቶም ፈፂሙ ኣይምለስን፡
2. ብምኽንያት ሓዳር ካብ ሰብ ሓዳር ንሓዲኦም ወይ ንክልቶኦም ካብ ሳልሳይ ወገን ተገይሩ ዝነበረ ውህብቶ ተስፋ ቃል ኣብ ልዕሊ'ቶም ውህብቶ ተስፋ ቃል ዝሃቡ ግቡእነት ኣየስዕብን፡፡

## ምዕራፍ ሽዱሽተ

## መርተዖ ሓዳር

### ዓንቀፅ 115 ስርዓት ኣቀራርባ መርትዖ ሓዳር

ሓዳር ምፍፃሙ ምርዳእ ዝከኣል ኣብዚ ምዕራፍ ብዝተመልከቱ መርትዖታት ጥራሕ'ዩ፡፡

### ዓንቀፅ 116 መረዳእታ ዕጩፍ ሓዳር

1. ሓዳር ምፍፃሙ ምርዳእ ዝከኣል ሓዳር ኣብ ዝተፈፀመሉ ዕለት ወይ ድሕሪኡ ብመሰረት ሕጊ ተዳሊዩ ዝተውሃበ ናይ ሓዳር መረዳእታ ምስክር ወረቐት ብምቕራብ እዩ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የፍቺ ሁኔታዎች

### አንቀጽ 113. ጠቅላላ ስርዓት

1. ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት አንቀጾች ያሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተጋቢዎቹ በተፋቱ ጊዜ የሀብታቸው ግንኙነት የሚጣራው ከሁለቱ አንዱ በሞተ ጊዜ የሚደረገው የንብረት ማጣራትና ማከፋፈል ስርዓት ዓይነት ይሆናል፤
2. በእነዚህ አንቀጾች ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በጋብቻው ውል ሆነ የጋብቻው ውል ከመፍረሱ በፊት ተጋቢዎቹ በሚያደርጉት በሌላ ዓይነት ስምምነት እንዲቀር ማድረግ አይቻልም፡፡

### አንቀጽ 114. በጋብቻ የቀረበ ስጦታና ጥቅም

1. በጋብቻ ምክንያት ከማንኛውም ወገን ለተጋቢዎቹ የሚሰጥ ስጦታና ጥቅም ጋብቻውን ጸንቶ ባለበት ጊዜ ይሁን ከፈረሰ በኋላ ስጦታውን ለሰጡ ሰዎች ወይም ለወራሾቻቸው በፍፁም አይመለስም፤
2. በጋብቻ ምክንያት ከተጋቢዎቹ ለአንዱ ወይም ለሁለቱም ከሶስተኛ ወገን ተደርጎ የነበረው የስጦታ ተስፋ ቃል በስጦታ ተስፋ ቃል ሰጪዎች ላይ ግዴታን አያስከትልም፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## የጋብቻ ማስረጃ

### አንቀጽ 115 የጋብቻ ማስረጃን ያቀራረብ ስርዓት

ጋብቻ መፈጸሙን ማስረዳት የሚቻለው በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ማስረጃዎች ብቻ ነው ፡፡

### አንቀጽ 116 የጋብቻ የጽሑፍ ማስረጃ

1. ጋብቻ መፈጸሙን ማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈጸመበት ዕለት ወይም ከዚያ በኋላ በሕጉ መሰረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com





2. እዚ ኣዋጅ ቅድሚ ምፅዳቑ ዝተፈፀሙ ሓዳር ብመሰረት ኣብ 1952 ዓ/ም ዝወፀ ሕጊ ፍትሃብሄር ኢትዮጵያን ሕጊ ቤተሰብ ትግራይ ኣዋጅ ቁፅሪ 33/91ን ዝቐርብ መርትዖ ሓዳር ተቐባልነት ይህልዎ፡፡

**ዓንቀፅ 117. ናይ ሓዳር ምስክር ወረቐት ኣብዘየለሉ እዋን ብዛዕባ ዝቐርብ መረዳእታ**

ከይተመዝገበ ዝተረፈ ሓዳር ወይ መዝገብ ብምጥፍኡ ምኽንያት ሓዳር ዝተፈፀመ ምዃኑ ብሓዳር ምስክር ወረቐት ምርዳእ ዘይተኻእለ እንተኾይኑ ሓዳር ንምፍፃሙን ኩነታት ሓዳር ምህላውን ብምርግጋፅ ምርዳእ ይከኣል፡፡

**ዓንቀፅ 118. ኩነታት ሓዳር ምህላው (1) ትርጉም**

ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ኩነታት ሓዳር ኣለዎም ዝበሃል ባዕሎም ከም ሰብኣይን ሰበይትን ዝቖፅሩን ዝነበሩን ካብ ምዃኖም ንላዕሊ ብኣዝማዶምን ብሕብረተሰብን ከም ሰብኣይን ሰበይትን ዝቕበልዎም ኮይኖም እንትርከቡ እዩ፡፡

**ዓንቀፅ 119.(2) ሓዳር ንምፍፃሙን ኩነታት ሓዳር ምህላውን ብዛዕባ ምርዳእ**

1. ብመሰረት ልዕል ክብል ብዝተመልከተ ዓንቀፅ 118 ሓደ ሰብ ብባዕሉን ምስ ባዕሉ ሓዳር ኣለኒ ምስ ዝበሎ ወገን ኩነታት ሓዳር ምህላው ምርዳእ ዝኽእል እንተኾይኑ፡ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሓዳር ተፈፂሙ እዩ ብምባል ሕጋዊ ግምት ይወስድ፡
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተመልከተ ግምት፡ ሓዳር ዘይምፍፃሙ ብዝኾነ ዓይነት ዘተኣማምን መረዳእታ ብምቕራብ ምፍራስ ይከኣል፡፡

**ምዕራፍ ሸውዓት**

**ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ብዛዕባ ምንባር**

**ዓንቀፅ 120 (1) ትርጉም**

ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ምንባር ማለት ሓደ ወድን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ብሕጊ ዝፀንዕ ዓይነት ሓዳር እንተይፈፀሙ ብመልክዕ ሓዳር እንትነብሩ ማለት'ዩ፡፡

2. ይህ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት ለተፈፀሙ ጋብቻዎች በ1952 ዓ/ም በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሃብሄር ሕግ እና በትግራይ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 33/91 ዓ/ም መሰረት የሚቀርብ ማስረጃ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀፅ 117. የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማይኖርበት ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ**

የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈጸሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ፣ ጋብቻ ለመፈጸሙና የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 118. የጋብቻ ሁኔታ መኖር (1) ትርጓሜ**

አንድ ወንድና አንዲት ሴት የጋብቻ ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሳቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተ ዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንዳባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡

**አንቀጽ 119. (2) ጋብቻ ስለመፈጸሙና የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ ስለማስረዳት**

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ 118 መሰረት አንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ ከሚለው ወገን ጋር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የህግ ግምት ይወስዳል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈጸሙን ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል፡፡

**ምዕራፍ ሰባት**

**ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

**አንቀጽ 120 (1) ትርጓሜ**

ጋብቻ ሳይፈጸሙ እንደባልና ሚስት መኖር ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በህግ በሚጸና አኳኃን ጋብቻ ሳይፈጽሙ በትዳር መልክ መኖሩ ማለት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com





### ዓንቀፅ 121. (2) <u>መብርሂ</u>

1. ሓዳር እንተይፈፀሙ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ይነብሩ ንምባል እቲ ወድን እታ ጓል ኣንስተይትን ዘርእዩዎ ኩነታት (ተግባራት) ብሕጊ ከም ዝተማራዓወ ዓይነት ሰባት ምኻኑ ኣድላይን ብቑዕን እዩ ፡፡
2. ንሳልሳይ ወገናት ክምዝተማራዓወ ኮይኖም ክቐርቡ ኣድላዪ ኣይኮነን፡
3. ሓደ ወድን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ብዝተፈለጠን ብዝተደጋገመን ዖታዊ ርክብ ምፍፃሞም ጥራሕ ኣብ መንጎ ክልቲኦም ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ርክብ ኣለዎም ንምባል ብቑዕ ምኽንያት ኣይኮነን ፡፡

### ዓንቀፅ 122. <u>ሓዳር ዝምድና ዘየስዕብ ብዛዕባ ምኻኑ</u>

1. ሓዳር እንተይፈፀሙ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ምንባር፡ ኣብ መንጎ ስጋ ኣዝማድ እቲ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይትን ከምኡ'ውን ኣብ መንጎ ስጋ ኣዝማድ እታ ጓል ኣንስተይትን ወዲ ተባዕታይን ዋላ ሓንቲ ናይ ሓዳር ዝምድና ኣየስዕብን፡
2. ኮይኑ ግና ዝምድና ሓዳር ኣብዘለሉ እዋን ንሓዳር ዝኽልክሉ ድንጋጌታት፡ ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ምንባር ኣብ ዝሀልወሉ እዋን'ውን ተፈፀምቲ ይኾኑ፡፡

### ዓንቀፅ 123. <u>ወፃኢታት ሓበሬዊ ናብረኦም ብዛዕባ ምሽፋን</u>

ሓዳር እንተይፈፀሙ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነበሩ ሰባት ወፃኢታት ሓባራዊ ናብረኦም ንምሽፋን ሕድሕዶም ክምዓቕምሞን ክእለቶምን ኣስተዋፅኦ ክገብሩ ኣለዎም፡፡

### ዓንቀፅ 124. <u>ብዛዕባ ሓባራዊ ሃፍቲ</u>

1. ብዛዕባ ንብረት ምምሕዳር ዝምልከት ዝገብሩዎ ውዕሊ ሕልው ኮይኑ፡ ሓዳር እንተይፈፀሙ ከምሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነበሩ ሰባት ንሰለስተ ዓመት ዘኣክል ሓቢሮም እንተነቢሮም፡ ሓቢሮም ኣብ ዝነበሩሉ እዋን ዘፍረዩዎ ንብረት ሓባራዊ ሃፍቶም ይኸውን፡፡

### አንቀጽ 121. (2) <u>ማብራሪያ</u>

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በህግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው፡

2. ለሶስተኛ ወገኖች እንዳተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም፡
3. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

### አንቀጽ 122. <u>የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ</u>

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየውና በሴቲቱ የስጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትዮዋና በወንድየው የስጋ ዘመዶች መካከል አንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም፡
2. ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለጊዜ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች፥ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለ ጊዜም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 123. <u>የጋራ ኑሮ ወጪያቸውን ስለመሸፈን</u>

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮኣቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው፡፡

### አንቀጽ 124. <u>ስለጋራ ሃብት</u>

1. የንብረት አስተዳደራቸው አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ለሶስት ዓመት ያክል አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ፡

www.abyssinialaw.com



2. ነዚ ዝፃባእ መረዳእታ ክሳብ ዘይቐረበ ሓቢሮም ኣብ ዝነብሩሉ ዝነብሮም ንብረት ሓቢሮም እንዳሃለዉ ከምዝተጠረዩ ሃፍቲታት ተገይሮም ይቑፀሩ፡

3. ሓዳር እንተይፈፀሙ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነበሩ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይትን ዘኣተውዎም ዕዳታት ሓቢሮም ኣብ ዝነብሩሉ እዋን ንሓባራዊ ናብረኦም ወይ ካብቲ ርክብ ንዝተወለዱ ቆልዑት መሰረታዊ ድሌት ንምምላእ ተባሂሉ ዝተኣተዉ ዕዳታት እንተኾኑ፡ ነቶም ዕዳታት ኣከፋፍላ ክልቲኦም ብሓባርን ብውልቀን ሓላፊነት ኣለዎም፡፡

## ዓንቀፅ 125. መሰል ምውራስ ዘየስዕብ ብዛዕባ ምዃኑ

ሓዳር እንተይፈፀሙ ከምሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነብሩ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይትን ኣብ ንንሕድሕዶም ዝኾነ ይኹን ዓይነት መሰል ምውራስ ዘስዕብ ኣይኮነን፡፡

## ዓንቀፅ 126. ሓባራዊ ንብረት ብዛዕባ ዘስዕቦ ውፅኢት

ኣብዚ ሕጊ ዓንቀፅ 124 ንኡስ ዓንቀፅ (1) ብዝተመልከተ መሰረት ሓባራዊ ሃፍቲ ኣብ ዝፍጠረሉ እዋን ብዛዕባ እቲ ንብረት ምምሕዳር፡ ኣከፋፍላ ዕዳ ሳልሳይ ወገንን ከይዲ ንብረት ምዕራይን ኣመልኪቱ ኣብዚ ሕጊ ኣብ ሓዳር ብዛዕባ ዝፍጠር ሓባራዊ ንብረትን ከይዲ ምዕራይን ዝተገለፁ ድንጋገታት (ዓንቀፅ 107-114) ተፈፃሚነት ይህልዎም፡፡

## ዓንቀፅ 127. ብዛዕባ ምውላድ ቆልዑት

ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ካብ ዝነብሩ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይትን ዝተወለዱ ቆልዑት ተወላድነቶም ዝረጋገፅ ኣብዚ ውሽጢ ሕጊ ብዛዕባ ተወላድነት ኣብ ዝብል ምዕራፍ ብዝተደንገገ መሰረት ይኸውን፡፡

## ዓንቀፅ 128. ብዛዕባ ርክብ ምቁራፅ

1. ሓዳር እንተይፈፀሙ ከምሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነበሩ ወዲ ተባዕታይን ጓል ኣንስተይትን ርክቦም ኣብ ዝኾነ እዋን ክቋረፅ ክገብሩ ይኽእሉ፡



2. ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖሯቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ እንደተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡

3. ጋብቻ ሳይፈጸሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው ዕዳዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ ዕዳዎች ሲሆኑ፡ ለዕዳዎች አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 125. የመውረስ መብት የማያስከትል ስለመሆኑ

ጋብቻ ሳይፈጸሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በመካከላቸው ማናቸውም ዓይነት የመውረስ መብት የሚያስከትል አይደለም፡፡

## አንቀጽ 126. የጋራ ንብረት ስለሚስከትለው ውጤት

በዚህ ህግ አንቀጽ 124 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር፡ የሶስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ህግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች (አንቀጽ 107-114) ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ 127. ልጆች ስለመወለድ

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱት ልጆች ተወላጅነታቸው የሚያረጋግጠው በዚህ ህግ ስለመወለድ በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 128. ግንኙነት ስለመቋረጥ

1. ጋብቻ ሳይፈጸሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲያቋረጥ ማድረግ ይችላሉ፣

www.abyssinialaw.com



2. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 124 ብዛዕባ ሓባራዊ ሃፍቲ ዝተገለፀ ሕልው ኮይኑ እቲ ርክብ ክቋረፅ ዝገበረ ወገን ጥፍኣት እንድሕር ዘይፈፂሙ ካሕሳ ክኸፍል ኣይግደድን፡፡

## ዓንቀፅ 129. ርክብ ብዛዕባ ምንባሮም ዝቐርብ መርትዖ

1. ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮኻ ብዛዕባ ምንባርን፥ ኩነታት ርክብ ምንባሩ ብምርግጋፅ ምርዳእ ይከኣል፣
2. ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ሓዳር እንተይፈፀሙ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ይነብሩ'ዮም ዝበሃል ብሕጋዊ መንገዲ ዝተኣተታወ እኳ እንተዘይኮኑ ከም ኩነታት ሰብ ሓዳር ኮይኖም እንትራኣዩን ብቤተሰቦምን ብሕብረተሰብን ከምዝተማራዓወ ሰባት ዝነብሩ'ዮም ኢሎም እንትግምትዎም እዩ፡፡
3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተመልከተ ኩነታት ምንባሩ ሓዲኡ ወገን ክረድእ እንተኽኢሉ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ዝነበሩ እዮም ብምባል ሕጋዊ ግምት ይወስድ፣
4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (3) ዝተመልከተ ሕጋዊ ግምት ብዝኾነ ዓይነት ዘተኣማምን መረዳእታ ብምቕራብ ርክብ ዘይምንባሩ ብምርዳእ ምፍራስ ይከኣል፡፡

## ዓንቀፅ 130. ሓዳር እንተይተፈፀመ ዝግበሩ ካልኦት ርክባት

1. ካብ ስርዓት ሓዳር ወይ ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ካብ ምንባር ወፃኢ ኣብ መንጎ ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ዝግበሩ ካልኦት ርክባት ኣብ ቅድሚ ሕጊ ምንም ዓይነት ውፅኢት ኣይህልዎምን፣
2. ኣብዚ ሕጊ ብዛዕባ ውላድ ጡብ ወይ ውላድ ብዛዕባ ምቕባል ዝተወሰኑ ድንጋጌታት ሕልዋት ኮይኖም ብኸምዚ ዓይነት ርክብ ዝተወለዱ ህፃናት ብዘይካ ምስ ኣዲኦም ምስ ካልእ ሰብ ዝኾነ ዓይነት ሕጋዊ ርክብ ኣይህልዎምን፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 124 ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሳ እንዲከፍል አይገደድም።

## አንቀጽ 129. ግንኙነት ስለመኖሩ የሚቀርብ ማስረጃ

1. ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር፣ የግንኙነቱ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል፣
2. አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳን በሕጋዊ መንገድ የተጋቡ ባይሆኑም እንደተጋቡ ሰዎች ሁኔታ ሆነው ሲታዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን አንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናቸው በማለት የህግ ግምት ይወስዳል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) የተመለከተውን የህግ ግምት ማናቸውም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ግንኙነት ያለመኖሩን በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል፡፡

## አንቀጽ 130. ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች

1. ከጋብቻ ስርዓት ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጪ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በህግ ፊት ምንም ዓይነት ውጤት አይኖራቸውም፡፡
2. በዚህ ህግ ስለጉድፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ህፃናት ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ህጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም፡፡

www.abyssinialaw.com





## ምዕራፍ ሸሞንተ

## ኣብ ሓዳርን ኣብ ፍትሕን ከምኡ'ውን ኣብ ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ብምንባር ዝለዓሉ ክርክራት ብዛዕባ ምውሳን

### ክፍሊ ሓደ

### ሓፈሻዊ

**ዓንቀፅ 131. ተፈፃምነት ብዛዕባ ዝህልዎ ሕጊ**

ኣብዚ ኣዋጅ ዝተመልከቱ ስነ-ስርዓት ድንጋገታት ሕልዋት ኮይኖም ኣብዚ ሕጊ ውሽጢ ኣብ ልዕሊ ዝተመልከቱ ዋኒናት ኣብ ዝለዓሉ ክርክራት ድንጋገታት ስነ-ስርዓት ፍትሃብሄር ሕጊ ኢትዮጵያ ተፈፃምነት ኣለዎም፡፡

**ዓንቀፅ 132. ብዛዕባ ምፅራይ ሃፍቲ ሰብኣይ ሰበይትን ዝተደንገጉ ተፈፀምቲ ምዃኖም**

1. ሓዳር ዝፈረሰ ብፍትሕ ዋላ እንተዘይኮነ ምዕራይ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን ዝምልከት ኣብዚ ሕጊ ምዕራፍ 5 ክፍሊ-ክልተ ዝተደንገገ ከከም ኣግባብነቶም ተፈፀምቲ ይኾኑ፡
2. ብፍላይ ሓዳር ዝፈረሰ ብምኽንያት ሞት ኣብ ዝኾነሉ እዋን ኣብ መንጎ ብህይወት ዘሎ በዓል ሓዳሩን ወረስቲ መዋትን ኣብ ንብረት ክፍፍል ብዝተመልከተ ክርክር እንትለዓል፡ ብዛዕባ ምዕራይ ሃፍቲ ሰብኣይን ሰበይትን ኣብ ምዕራፍ 5 ክፍሊ ክልተ እዚ ሕጊ ዝተደንገገ ከከም ኣግባብነቶም ተፈፀምቲ ይኾኑ፡፡

**ዓንቀፅ 133. ብዛዕባ ክርክር ሰብኣይን ሰበይትን ዝረኣየሉ ኣግባብ**

ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ክርክር ሰብኣይን ሰበይትን ኣብዝርእየሉ እዋን ከምኩነታቱ ኣድላይ ኮይኑ እንትረኸቦ፡ ሰብኣይን ሰበይትን ብሓባር ወይ ነንሕድ ሕዶም እንትዘራርብ፡ ወይ ነቲ ዋኒን እንትምርምርን ምስክር እንትሰምዕን ብዕፅው መጋባእያ ይኸውን፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## በጋብቻ እና በፍቺ እንዲሁም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 131. ተፈፃሚነት ስለሚኖረው ህግ**

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት የስነ-ስርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ህግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 132. የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው**

1. ጋብቻ የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ 5 ክፍል ሁለት የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡
2. በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በህይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ፡ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት በዚህ ህግ በምዕራፍ 5 ክፍል ሁለት ላይ የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 133. የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ**

ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፡ ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ችሎት ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com



**ዓንቀፅ 134. ብዛዕባ ኣወሃህባ ውሳነ**

ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣድላይን ግቡእን ኮይኑ እንትርኸቦ ፍትሕ ኣብ ዝውሰነሉ እዋን ናይቶም ሰብ ሓዳርን ወይ ኣዝማዶምን ፅቡቕ ሽም ንምሕላው ዝርዝር ጉዳያት ካብ ምቅላዕ ብምቑጣብ ውሳነ ፍትሕ ንምሃብ ዘኽእሉ ምኽንያታት ምህላዎም ጥራሕ ኣብ ውሳኒኡ ክስፍር ይኽእል፡፡

**ዓንቀፅ 135. ብዛዕባ ይግባኣኒ**

ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ፍትሕ ምውሳኑ ጥራሕ መሰረት ብምግባር ይግበኣኒ ምሕታት ኣይከኣልን፡፡

**ዓንቀፅ 136. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ብዛዕባ ህፃናት ኣተሓሳድዋን ኣታሓሕዛን ብዝምልከት ዝህቦ ውሳነ**

1. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ሓዳር ክፈርስ እንትውሰን ህፃናት ምስ መን ክነብሩ ከምዝግባእ፣ ብዛዕባ ትምህርቶምን ኣተሓሳልዋ ጥዕንኦምን፣ ብዛዕባ ቀለቦምን ብሓፈሻ ብዛዕባ ኣነባብረኦምን ከምኡ'ውን ወለድን ደቆምን ክጠያየቑ ብዛዕባ ዘለዎም መሰል ክውስን ኣለዎ፡፡
2. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ብዝተመልከተ ኩነታት ውሳነ ኣብ ዝህበሉ እዋን ናይ ወለዲ ኣታዊ፣ ዕድመ፣ ጥዕናን ኩነታት መነባብሮን ከምኡ'ውን ዕድመ ህፃናትን ጥቕሞምን ድሌቶምን ዝሕለወሉ ኩነታት ክገናዝብ ኣለዎ፡፡
3. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ብዛዕባ ህፃናት ኣታሓሕዛን ኣተሓሳልዋን ዝሀቦ ውሳነ ብምኽንያት ምልውዋጥ ኩነታት ብምግባር ዝቐርብ ሕቶ ክማሓየሽ ወይ ክልወጥ ይኽእል ፡፡

**ዓንቀፅ 137. ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ብዛዕባ ምንባር**

ኣብዚ ክፍሊ ዝተመልከቱ ድንጋጌታት ከከም ኣግባብነቶም ኣብ ልዕሊ ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ኣብ ዝነብሩ ሰባት'ውን ተፈፃምቲ ይኾኑ፡፡



**አንቀጽ 134. ስለውሳኔ አሰጣጥ**

ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ በሚወሰንበት ጊዜ የተጋቢዎችን ወይም የዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመተቸት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሳኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 135. ስለይግባኝ**

ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሰረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 136. የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሳኔ**

1. ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ጋብቻውን እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፣ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ ስለቀለባቸውና ባጠቃላይ ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት፣
2. ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ሁኔታ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆችን የገቢ፣ የዕድሜ፣ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን ዕድሜ፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበት ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል፣
3. ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 137. ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

www.abyssinialaw.com



### ክፍሊ ክልተ

### ብዛዕባ ስልጣን ቤት ፍርዲ

**ዓንቀፅ 138. ዝፀንዕ ሓዳር ምህላው**

1. ሓዳር ዝተፈፀመ ወይ ዝፀንዕ ብዛዕባ ምዃኑ ክርክር እንድሕር ተላዒሉ ነቲ ዋኒን ሪኡ ክውስን ስልጣን ዝህልዎ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥራሕ እዩ።
2. ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ማለት ብኣዋጅ ቁፅሪ 32/1990 ዝተጣየሸ ቤት ፍርዲ እዩ።

**ዓንቀፅ 139. ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ምንባር**

1. ኣብ መንጎ ሓደ ወዲ ተባዕታይን ሓንቲ ጓል ኣንስተይትን ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ምንባር ርክብ ብዛዕባ ምንባሩ ክርክር እንድሕር ተላዒሉ ነቲ ዋኒን ሪኡ ክውስን ስልጣን ዝህልዎ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥራሕ'ዩ።
2. ከምኡ'ውን ብምኽንያት እዚ ርክብ ንዝለዓሉ ሞጎታት ውሳነ ዝህብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥራሕ እዩ።

**ዓንቀፅ 140. ሕቶ ፍትሒ፣ ብምኽንያት ፍትሒ ዝለዓሉ ክትዓት ፍትሒ ንምፍፃሙ ምርግጋፅን**

1. ብሰብኣይን ሰበይትን ወይ ካብ ክልቲኦም ብሓዲኦም ዝቐርብ ሕቶ ፍትሕ ንክውሰን ዝቐርብ ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ጥራሕ እዩ፣
2. ብምኽንያት ፍትሕ ዝለዓል ክትዕ ዝቐርብ ናብቲ ውሳነ ፍትሕ ዝሃበ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ'ዩ።
3. ውሳነ ፍትሕ ዝተውሃበ ምዃኑን ዘይምዃኑን ምርግጋፅ ዝኽእል ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ'ዩ።

**ዓንቀፅ 141. ኣብ ውሽጢ ሓዳር ዝፍጠር ዘይምርድዳእ**

1. ኣብ መንጎ ሰብኣይን ሰበይትን ኣብ ውሽጢ ሓዳር ዝለዓሉ ፀገማት መርሚሮም ዳይነት ዝህቡ ኣብቲ ሰብኣይን ሰበይትን ዝነብሩሉ ዝርከቡ ዳያኑ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እዮም፣



### 2. ክፍል ሁለት

### ስለፍርድ ቤት ስልጣን

**አንቀጽ 138. የሚጸና ጋብቻ ስለመኖሩ**

1. ጋብቻ የተፈጸመ ወይም የሚጸና ስለመሆኑ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ብቻ ነው።
2. ማህበራዊ ፍርድ ቤት ማለት በአዋጅ ቁጥር 32/1990 የተቋቋመ ፍርድ ቤት ነው።

**አንቀጽ 139. ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር**

1. በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣
2. እንዲሁም በዚህ ግንኙነት ምክንያት ለሚነሱ ክርክሮች ውሳኔ የሚሰጠው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ 140. የፍቺ ጥያቄ፣ በፍቺ ምክንያት የሚነሱ ክርክሮችና ፍቺ መፈጸሙን ማረጋገጥ**

1. በባልና ሚስት ወይም ከሁለቱ በአንደኛው የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ እንዲወሰን የሚቀርበው ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣
2. በፍቺ ምክንያት የሚነሳ ክርክር የሚቀርበው ወደ የፍቺ ውሳኔ ለሰጠው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ነው፣
3. የፍቺ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ነው።

**አንቀጽ 141. በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች**

1. በባልና ሚስት መካከል በትዳራቸው ውስጥ የሚነሱ ችግሮች መርምረው ዳኝነት የሚሰጡ ባልና ሚስት በሚኖሩበት ቦታ የሚገኙ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ናቸው፣

www.abyssinialaw.com





2. ሰብኣይን ሰበይቲን ጉዳዮም ብውልቀ ብዝመረፅዎም ሽማግለታት ክረኣየሎም እንተደልዮም ግና ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተገለፀ ድንጋገ ዝኽልክሎም ኣይኮነን፡፡

ዓንቀፅ 142. ብምኽንያት ሞት ዝፈርስ ሓዳር

ሓዳር ዝፈረሰ ብምኽንያት ሞት ሰብኣይ ወይ ሰበይቲ ኣብ ዝኾነሉ እዋን ነዚ ስዒቡ ዝለዓል ክትዕ ዝቐርብ ናብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እዩ፡፡ ከምኡ' ውን ነዚ መርሚሩ ውሳነ ክህብ ስልጣን ዘለዎ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እዩ፡፡

ምዕራፍ ትሻዓተ

ብዛዕባ ሓዳር ምዝገባ

ዓንቀፅ 143. ዓይነት መርትዖ ሓዳር

1. ሓዳር ዝተፈፀመ ምዃኑ ዘጠራጥር ወይ ዘካትዕ ክይኑ እንትርከብ ምስክር ወረቐት ሓዳር ምዝገባ ብምቕራብ ይረጋገፅ፡
2. ምስክር ወረቐት ሓዳር ምዝገባ እንተጠፊኡ ብቶም ኣብቲ ምዝገባ ምስክር ወረቐት ሓዳር ዝፈረሙ መሰኻኽር ወይ ነቲ ሓዳር ዝመዝገበ ሰራሕተኛ ብምምስካር ሓዳር ዝተፈፀመ ምዃኑ ምርግጋፅ ይከኣል፡፡

ክፍሊ ሓደ

ኣመዳድባ ሰራሕተኛታት ምዝገባ ሓዳር

ዓንቀፅ 144. ብብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝምደቡ ብዛዕባ ምኳኖም

1. ብብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝምደቡ ሰራሕተኛታት ምዝገባ ሓዳር መንግስቲ ኣድላይ እዩ ኣብ ዝበሎ ቦታ ቤት ፅሕፈት ክጣየሽ ይኽእል፡
2. ኣብ ሕድ ሕድ ቤት ፅሕፈት ዝምደቡ ዋናን ሓገዝን ሰራሕተኛታት ሓዳር ምዝገባ እንትህልዉ፣ ዋና ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ ብዝኾነ ምኽንያት ኣብ ስርሑ ኣብዘይርከበሉ እዋን ሓጋዚ ሰራሕተኛ ሓዳር ምዝገባ ተተኪኡ ይሰርሕ፡

2. ባልና ሚስት ጉዳያቸው በግል በመረጥዋቸው ሽማግሌዎች እንዲታይላቸው ከፈለጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ድንጋጌ የሚከለክላቸው አይሆንም፡፡

አንቀጽ 142. በሞት ምክንያት የሚፈርስ ጋብቻ

ጋብቻ የፈረሰው በባል ወይም ሚስት ሞት ምክንያት በሆነበት ጊዜ ይህን ተከትሎ የሚነሳ ክርክር የሚቀርበው ወደ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ነው፡፡ እንዲሁም ይህንን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ነው፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ

ስለጋብቻ ምዝገባ

አንቀጽ 143. የጋብቻ ማስረጃ ዓይነት

1. ጋብቻ የተፈጸመ ለመሆኑ የሚያጠራጥር ወይም የሚያከራክር ሆኖ ሲገኝ የጋብቻ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል፡
2. የጋብቻ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ከጠፋ በጋብቻ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የፈረሙ ምስክሮች ወይም ጋብቻውን የመዘገበ ሰራተኛ በማስመስከር ጋብቻ የተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ክፍል አንድ

የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኞች ስለመዳደብ

አንቀጽ 144. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስለመመደባቸው

1. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚመደቡ የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኞች መንግስት አስፈላጊ ነው በሚለው ቦታ የጋብቻ ምዝገባ ጽህፈት ቤት ሊያቋቁም ይችላል፣
2. በእያንዳንዱ ጽህፈት ቤት የሚመደቡ ዋና እና ረዳት የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኞች ሲኖሩ፣ ዋና የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በሆነ ምክንያት በስራ ገበታው በማይገኝበት ጊዜ ረዳት የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛው ተተክቶ ይሰራል፣

www.abyssinialaw.com



3. እቲ ዋና ሰራሕተኛ ሓዳር ምዝገባ ኣብ ዘይህልወሉ እዋን ሓጋዚ ሰራሕተኛ ሓዳር ምዝገባ ዝፍፅሞ ምዝገባ ማዕረ ተቐባልነትን ዋጋን ይህልዎ፣
4. ብሂራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ኣድላዪ ኮይኑ እንትረኽቦ ስራሕቲ ሓዳር ምዝገባ ኣግባብ ኣለዎ ንዝብሎ ቢሮ ወይ ቤት ፅሕፈት ብሓላፊነት ክህቦ ይኽእል'ዩ፡፡

## ዓንቀፅ 145. ብዛዕባ ምዝገባ ፍትሕ፣ ልደትን ሞትን

ምዝገባ ፍትሕ፣ ልደትን ሞትን ኣብ ኣንቀፅ 144 ብዝተጠቀሰ ሰራሕተኛ ምዝገባ ሓዳር ብተመሳሳሊ ኣግባብ ዝፍፀም ይኸውን፡፡

## ክፍሊ ክልተ

## ተግባር ሰራሕተኛ ሓዳር ምዝገባ

### ዓንቀፅ 146. መትከል

1. ተግባር ሰራሕተኛ ሓዳር ምዝገባ ኣብቲ ዝተመደበሉ ቤት ፅሕፈት ዝፍፀም ሓዳር ምምዝጋብን ሰነዳት ዓቒብካ ምቕማጥን'ዩ ፡
2. ሰብ ሓዳር ወይ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝሓትዎ እዋን ትኽክለኛ ቅዳሕ ሓዳር ምዝገባ ይህብ፡፡

### ዓንቀፅ 147. ኣታሓሕዛ ሰነድ ምዝገባ

ኣብ ሕድ ሕድ ቤት ፅሕፈት ዝምደቡ ሰራሕተኛታት ምዝገባ ሓዳር ነዚ ስራሕ ጥራሕ ዝውዕል ዝተፈለየ መዝገብ ይህልዎም፡፡

### ዓንቀፅ 148. ሰነድ ሓዳር ምዝገባ ክሕዞም ዝግባእ ዝርዝር ነገራት

1. ሙሉእ ሽም ሰብኣይን ሰበይትን፣ ዝተወለድሉ ዕለትን ቦታን፣
2. ሓዳር እንትፍፀም ዝነበሩ መሰኻኽር ሽም፣
3. ሓዳር ዝተፈፀመሉ ቦታ፣
4. ሓዳር ዝተፈፀመሉ ዕለትን ዓመተ ምህረትን፣
5. ሽምን ፊርማን ስነ-ስርዓት ሓዳር እንትፍፀም ወይ ብድሕሪኡ ንቶም ተማራዓውትን መሰኻኽርን ተቐቢሉ ዘፈራረሞም ሰራሕተኛ ምዝገባ ሓዳር፡፡



3. ዋናው የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛ በማይኖርበት ጊዜ ረዳት የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛው የሚያከናውነው ምዝገባ እኩል ተቀባይነትና ዋጋ ይኖረዋል፣
4. የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጋብቻ ምዝገባ ስራዎች አግባብነት አለው ለሚለው ቢሮ ወይም ጽህፈት ቤት በኃላፊነት ሊሰጠው ይችላል፡፡

## አንቀፅ 145. ስለፍቺ፣ ልደትና ሞት ምዝገባ

የፍቺ፣ ልደትና ሞት ምዝገባ በአንቀፅ 144 በተጠቀሰው የጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ በተመሳሳይ አገባብ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛ ተግባር

### አንቀፅ 146. መሰረቱ

1. የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛ ተግባር በተመደበበት ጽህፈት ቤት የሚፈጸምውን ጋብቻ መመዝገብና ሰነዶች ጠብቆ ማስቀመጥ ነው፣
2. ተጋቢዎች ወይም ፍርድ ቤት በሚጠይቁት ጊዜ የጋብቻ ምዝገባው ትክክለኛና ቅጅ ይሰጣል፡፡

### አንቀፅ 147. የምዝገባ ሰነድ አያያዝ

በእያንዳንዱ ጽህፈት ቤት የሚመደቡ የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኞች ለዚሁ ስራ ብቻ የሚውል የተለየ መዝገብ ይኖራቸዋል፡፡

### አንቀፅ 148. የጋብቻ ምዝገባ ሰነድ ሊይዛቸው የሚገባ ዝርዝር ነገሮች

1. የባልና ሚስት ሙሉ ስም፣ የተወለዱበት ዕለትና ቦታ፣
2. ጋብቻው ሲፈጸም የነበሩ ምስክሮች ስም፣
3. ጋብቻው የተፈጸመበት ቦታ፣
4. ጋብቻው የተፈጸመበት ዕለትና ዓመተ ምህረት፣
5. የጋብቻው ስነ-ስርዓት ሲፈጸም ወይም ከዛ በኋላ ተጋቢዎቹንና ምስክሮቹን ተቀብሎ ያፈራረማቸው የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛ ስምና ፊርማ፣

www.abyssinialaw.com



## ዓንቀፅ 149. ዝተፈፀመ ሓዳር ዝምዝገበሉ እዋን

1. ብዝኾነ ስርዓት ሓዳር ዝፈፀሙ ሰብኣይን ሰበይትን ኣብቲ ሓዳር ዝተፈፀመሉ ዕለት ወይ ድሕሪኡ ኣብ ሓዳር ዝተፈፀመሉ ቦታ ወይ ኣብዝነብርሉ ቦታ ናብ ዝርከብ ቤት ፅሕፈት ሓዳር ምዝገባ ብኣካል ብምቕራብ ክምዝገቡ ኣለዎም፡፡
2. ኣብ ንኡስ ኣንቀፅ 1 ዝተጠቐሰ ሕልው ኮይኑ እቲ ምዝገባ ዝካየድ ሓዳር ካብዝተፈፀመሉ ዕለት ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ ሽድሽተ ወርሒ ጥራሕ ክኸውን ኣለዎ፡፡

## ዓንቀፅ 150. ተቐባልነት ሓዳር

ኣብ ቤት ፅሕፈት ሓዳር ምዝገባ ቀሪቡ ሕጋዊ መዐቀኒታት ኣማሊኡ ዝተመዝገበ ሓዳር ሙሉእ ተቐባልነት ኣለዎ፡፡

## ዓንቀፅ 151. ግቡእ ሓዳር መዝጋቢ ሰራሕተኛ

1. ኣብ ኢዱ ዝርከቡ ሰነዳት ሓዳር ምዝገባ ብግቡእን ብጥንቃቐን ምሓዝ፣
2. ኣብ ሓለውኡ ዝርከቡ ሰነዳት ሓዳር ምዝገባ ብሕጊ ኣብ ዝተወሰነሉ እዋን ውሽጢ ናብ ብልዕሊኡ ዘሎ ሓዳር ምዝገባ መሓውር ምትሕልላፍ፣
3. ኣብ ኢዱ ዝርከቡ ሰነዳት ምዝገባ ሓዳር ብተፈጥሮ ይኹን ብኻልኦት ምኽንያታት ጉድኣት እንተበፂሖዎም ብቕልጡፍ ናብ ብልዕሊኡ ዘሎ ኣካል ሪፖርት ምግባር፣
4. ኣብ መንጎ ተመራዓውቲ ፡-
   ሀ) ካሊእ ስሩዕ ሓዳር ዘይብሎም ምዃኖም፣
   ለ) ዝምድና ስጋ ወይ ሓዳር ዘይብሎም ምዃኖም፣
   ሐ) ተመራዓውቲ ዕድሚኦም 18 ዓመት ዝመልአ ምዃኑ፣
   መ) ተመራዓውቲ ብኣካል ዝቐረቡ ምዃኖምን፣
   ረ) መሰኻኽር ኣብ ቅድሚ ተመራዓውቲ ምስክርነቶም ዝሃቡ ምዃኖም ናይ ምርግጋፅ ሓላፊነት ኣለዎ፡፡

## ዓንቀፅ 152. ቅፅዓት

ኣብዚ ምዕራፍ ዝተደንገጉ ሕጊታት ብምትሕልላፍ ስራሕቲ ሓዳር ምዝገባ ኣብ ልዕሊ ዝፈፀሙ ስራሕተኛታት ምዝገባ ሓዳር ኣብ መቕፅዒ ሕጊ ገበን ዝተደንገጉ ቅፅዓታት ተፈፀምቲ ይኾኑ፡፡

## አንቀጽ 149. የተፈጸመው ጋብቻ የሚመዘገብበት ጊዜ

1. በማንኛውም ስርዓት ጋብቻ የፈጸሙ ባልና ሚስት ጋብቻ በተፈጸመበት ዕለት ወይም ከዛ በኃላ ጋብቻ በተፈጸመበት ቦታ ወይም በሚኖሩበት ቦታ ወደሚገኘው የጋብቻ ምዝገባ ጽህፈት ቤት በአካል በመቅረብ መመዝገብ አለባቸው፡፡
2. በንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ምዝገባው የሚካሄደው ጋብቻው ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 150. የጋብቻው ተቀባይነት

በጋብቻ ምዝገባ ጽህፈት ቤት ቀርቦ ሕጋዊ መስፈርቶችን አሟልቶ የተመዘገበ ጋብቻ ሙሉ ተቀባይነት አለው፡፡

## አንቀጽ 151. የጋብቻ ምዝገባ ሰራተኛ ግዴታ

1. በእጁ ላይ የሚገኙትን የጋብቻ ምዝገባ ሰነዶች በተገቢውና በጥንቃቄ መያዝ ፣
2. በእርሱ ጥበቃ የሚገኙትን የጋብቻ ምዝገባ ሰነዶች በህግ በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ ከእርሱ በላይ ወደአለው የጋብቻ መዝጋቢ አካል ማስተላለፍ፣
3. በእጁ የሚገኙትን የጋብቻ ምዝገባ ሰነዶች በተፈጥሮ ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ጉዳት ቢደርስባቸው በፍጥነት ለበላይ አካል ሪፖርት ማድረግ፣
4. በተጋቢዎቹ መካከል፡-

ሀ. ሌላ መደበኛ ጋብቻ የሌላቸው መሆኑን፣
ለ. የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው መሆኑን፣
ሐ.ተጋቢዎቹ ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሞላው መሆኑን፣
መ. ተጋቢዎቹ በአካል የቀረቡ መሆናቸውን፣
ሠ. ምስክሮች በተጋቢዎች ፊት ምስክርነታቸው የሰጡ መሆናቸው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 152. ቅጣት

በዚህ ምዕራፍ የተደነገጉ ሕጎች በመተላለፍ የጋብቻ ምዝገባ ስራዎች የፈጸሙ የጋብቻ ምዝገባ ስራተኞች ላይ በወንጀል ህግ የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

www.abyssinialaw.com





## ምዕራፍ ዓሰርተ

## ብዛዕባ ተወሳድነት

### ክፍሊ ሓደ

### ኣቦነትን ኣደነትን ብዛዕባ ምፍላጥ

### ንኡስ ክፍሊ ሓደ

### ሓፈሻዊ ድንጋገ

**ዓንቀፅ 153. ናይዚ ሕጊ ድንጋገታት መገደድቲ ብዛዕባ ምዃኖም**

እቲ ሕጊ ብግልፂ ዝፈቅድ እንተዘይኮይኑ ብዛዕባ ምፍላጥ ኣቦነትን ኣደነትን ኣብዚ ሕጊ ዝተመልከቱ ድንጋገታት ብስምምዕነት ክልወጡ ኣይኽእሉን፡፡

**ዓንቀፅ 154. ብዛዕባ ምርግጋፅ ኣደነት**

ኣዶ ዝተበሃለት ሰበይቲ ነቲ ቆልዓ ብምውላዳ ጥራሕ ኣዶነታ ይረጋገፅ፡፡

**ዓንቀፅ 155. ብዛዕባ ምርግጋፅ ኣቦነት**

1. እቲ ቆልዓ ኣብዝተጠነሰሉ ወይ ኣብ ዝተወለድሉ እዋን ኣብ መንጎ እታ ኣደን ሓደ ወዲ ተባዕታይን ብሕጊ ዝተፈለጠ ርክብ ምንባሩ ብምርግጋፁ ምኽንያት ኣቦነት ይረጋገፅ፣
2. ኣቦ ነቲ ቆልዓ ውላደይ እዩ ኢሉ ብምቕባሉ ምኽንያት ኣቦነት ክረጋገፅ ይኽእል፣
3. ብማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ብዝውሃብ ውሳነ'ውን ኣቦነት ክፍለጥ ምግባር ይከኣል፡፡

### ንኡስ ክፍሊ ክልተ

### ኣቦነት ብሕጊ ግምት ዝፍለጥ ብዛዕባ ምዃኑ

**ዓንቀፅ 156. በዓል ሓዳር ኣቦ'ዩ ተባሂሉ ዝግመት ብዛዕባ ምዃኑ**

ኣብ ውሽጢ ሓዳር ዝተጠነሰ ወይ ዝተወለደ ቆልዓ ኣቡኡ እዩ ዝበሃል እቲ በዓል ሓዳራ እዩ ፡፡

**ዓንቀፅ 157. ሓፈሻዊነት እቲ ግምት**

1. ህፃን ምስ ኣዶ ዘለዎ ርክብ ብዝኾነ ኩነታት ዝተረጋገፀ ዋላ እኳ እንተኾነ ኣብ ዓንቀፅ 155 ዝተመልከተ ድንጋገ ተፈፃምነት ይህልዎ፣

## ምዕራፍ አስር

## ስለመወለድ

### ክፍል አንድ

### አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### አጠቃላይ ድንጋጌ

**አንቀጽ 153. የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው**

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትና እናትነትን ስለማወቅ የተመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 154. እናትነትን ስለማረጋገጥ**

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነቷ ይረጋገጣል፡፡

**አንቀጽ 155. አባትነት ስለማረጋገጥ**

1. ልጁ በሚጸነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩን በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይረጋገጣል፣
2. አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ሊረጋገጥ ይችላል፣
3. በማሕበራዊ ፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

### ንዑስ ክፍል ሁለት

### አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

**አንቀጽ 156. ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ**

በጋብቻ ውስጥ የተጸነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው፡፡

**አንቀጽ 157. የግምቱ አጠቃላይነት**

1. ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም በአንቀጽ 155 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚት ይኖረዋል፣

www.abyssinialaw.com



2. ናይቲ ቆልዓ ናይ ልደት ምስክር ወረቐት እቲ በዓል ሓዳራ ንእዲኡ ኣቦ ዘይምዃኑ ወይ ኣቦ እቲ ቆልዓ ካሊእ ሰብ ምዃኑ ዘመላኽት ዋላኳ እንተኾነ እዚ ድንጋገ ተፈፃምነት ይህልዎ፣
2. ልዕል ክብሊ ዝተመልከተ ኩነታት ኣብ ዘጋጠመ እዋን እቲ ናይ ልደት ምስክር ወረቐት ክእረም ይግበር፡፡

ዓንቀፅ 158. ጥንሲ ብዛዕባ ዝፀንሓሉ እዋን

1. ሓዳር ካብ ዝተፈፀመ ድሕሪ 90 መዓልቲታት ወይ ሓዳር ምስፈረሰ ኣብ ውሽጢ 300 መዓልቲታት ዝተወለደ እንተኾይኑ እቲ ቆልዓ ኣብ ውሽጢ ሓዳር ከምዝተጠነሰ ይቑፀር፣
2. ነዚ ተፃባኢ ዝኾነ መርትዖ ተቐባልነት ኣይህልዎን፡፡

ዓንቀፅ 159. በዓል ሓዳር ምጥፋእ

ኣብዚ ኣዋጅ ብዛዕባ ኣቦነት ዝተደንገገ ናይ ሕጊ ግምታት "ብሕጊ ኣቦ እዩ" ዝተብሃለ ሰብ ምጥፋእ ብፍርዲ ካብ ዝተነገረ እዋን ብዛዕባ ምንባሩ ወረ ካብዝተሰምዐሉ ዕለት ናይ መወዳእታ እዩ ካብ ዝተባሃለሉ ድሕሪ 300 ማዓልቲታት ንዝተወለደ ቆልዓ ተፈፃምነት ኣይህልዎን፡፡

ዓንቀፅ 160. ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢርካ ብምንባር ብዛዕባ ዝተወለደ ቆልዓ

1. ሓዳር እንተይተፈፀመ ከም ሰብኣይን ሰበይትን ሓቢሮም ኣብ ዝነብሩ እዋን ዝተጠነሰ ወይ ዝተወለደ ቆልዓ ኣቡኡ በዚ ርክብ ምስ ኣዲኡ ሓቢሩ ዝነብር ሰብ እዩ፡፡
2. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 156ን 157ን ዝተመልከቱ ድንጋገታት ኣብዚ ዓንቀፅ ንዝተመልከተ ሕጋዊ ግምት'ውን ተፈፃምነት ኣለዎም፡፡

ንኡስ ክፍሊ ሰለስተ
ውላድ ብዛዕባ ምቕባል

ዓንቀፅ 161. (1) መትከል

ብመሰረት ልዕል ክብሉ ዝተመልከቱ ድንጋገታት ኣቦኡ ነቲ ቆልዓ ክፍለጥ እንድሕር ዘይተኻኢሉ ኣቦ "ውላደይ'ዩ" ኢሉ ብምቕባሉ ክፍለጥ ይከኣል፡፡



2. የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጅ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመላክት ቢሆንም እንኳን ይኸው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፣
3. ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት የምስክርት ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 158. እርግዝናው ስለሚቆጸበት ጊዜ

1. ጋብቻው ከተፈጸመ ከ90 ቀናት በኃላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ፣ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተጸነሰ ይቆጠራል፡፡
2. ለዚህ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 159. የባልየው መጥፋት

በዚህ አዋጅ ስለአባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች "በሕግ አባት ነው" የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ300 ቀናት በኃላ የተወለደ ልጅ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 160. ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ስለተወለደ ልጅ

1. ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተጸነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ በዚህ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው፣
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 156 እና 157 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው የህግ ግምትም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት
ልጅነትን ስለመቀበል

አንቀጽ 161. (1) መሰረቱ

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ አባትየው "ልጄ ነው" ሲል በመቀበሉ ሊታወቅ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com



3. ወለዲ ኣዶ እቲ ቆልዓ ኣብዘይህልወሉ እዋን ንሳዕሊ ዝቑፀር ካሊእ ወላዲ ወይ ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ እንተኾይኑ ድማ ብመማሓዳሪኡ ክወሃብ ይክእል፡፡

## ዓንቀፅ 167. ብዛዕባ እቲ ቆልዓ ንኣካለ መጠን ምብፃሕ

ኣቦ'ቲ ቆልዓ ንውላዱ ዝተቐበሎ ንኣካለ መጠን ድሕሪ ምብፅሑ እንተኾይኑ ኣቦ ነቲ ቆልዓ ምቕባሉ ውፅኢት ዝረክብ እቲ ቆልዓ ነቲ ኣቦነት ዝተቐበሎ እንተኾይኑ'ዩ ፡፡

## ዓንቀፅ 168. ኩነታት ኣሚንካ ምቕባል

ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 165 ን 166ን ዝተመለከቱ ሰባት ተግባር ኣቦነት ምቕባል ምፍፃሙ ካብዝፈለጡሉ ዕለት ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ ሓደ ወርሒ መቃወሚ ክርክር እንተዘይኣሊዒሎም ኣሚኖም ከምተቐበሉዎ ይቑፀር፡፡

## ዓንቀፅ 169. ብዛዕባ ምማት ቆልዓ

እቲ ቆልዓ ናብ ታሕቲ ዝቑፀሩ ተወለድቲ ተኪኡ እንተዘይሞይቱ ተወላድነቱ ኣሚንካ ምቕባል ኣይከኣልን፡፡

## ዓንቀፅ 170. ብዛዕባ ምስዓር ቃል

1. ኣቦ ውላደይ እዩ ኢሉ ንዝሃቦ ቃል ምስዓር ኣይከኣልን፡
2. መማሓደሪኡ ቅድም ክብል ስምምዕነቱ ሂቡ እንተዘይኮይኑ ውላደይ'ዩ ኢሉ ዝተቐበለ ኣካለ መጠን ዘይበፅሐ ቆልዓ ቅድሚ ኣካለ መጠን ምብፅሑን ድሕሪ ንኣካለ መጠን ምብፅሑን'ውን ክሳብ ሓደ ዓመት "ውላደይ'ዩ" ኢሉ ንዝሃቦ ቃል ክስዕሮ ይኽእል፡፡
3. ውላደይ እዩ ክብል ንዝተቐበሎ ቃል ንምስዓር ብሕጋዊ መሰል ዘለዎ እቲ ኣካለ መጠን ዘይበፅሐ ቆልዓ ጥራሕ እዩ፡፡ ሕጋዊ ወኪላት እቲ ቆልዓ ኮኑ ወረስቱ በዚ መሰል ክጥቀሙ ኣይኽእሉን፡፡

## ዓንቀፅ 171. ብዛዕባ ምፍራስ

1. ውላድ ብዛዕባ ምቕባል ዝተነገረ ቃል ብሓይሊ ዝተውሃበ ምኻኑ ብምርዳእ ክፈርስ ይኽእል፡



3. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ፣ ወደ ላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ፣ ወይም በፍርድ የተከለከለ ሰው ከሆነ ደግሞ አሳዳሪው ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16 . ስለልጁ ለአካለ መጠን መድረስ

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኃላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉን ውጤት የሚገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው፡፡

## አንቀጽ 168. አምኖ የመቀበል ሁኔታ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 165 እና 166 የተመለከቱት ሰዎች፣ የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመቃወሚያ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ አምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል፡፡

## አንቀጽ 169. የልጅ መሞት

ልጅየው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር፣ ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይቻልም፡፡

## አንቀጽ 170. ቃሉን ስለመሻር

1. ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይቻልም፡
2. አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር፣ ልጅነትን የተቀበለ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አካለ መጠን ከመድረሱ በፊት እና አካለ መጠን ከደረሰ በኃላም እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ድረስ "ልጄ ነው" ሲል የሰጠውን ቃል ሊሽር ይችላል፡፡
3. ልጄ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾቹ በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 171. ስለማፍረስ

1. ልጅነት ለመቀበል የተነገረ ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com





ዓንቀፅ 162. (2) ትርጉም

1. ሓደ ሰብ ንሓደ ዝተጠነሰ ወይ ንዝተወለደ ቆልዓ ውላዱ ምዃኑ ዝፍለጥ "ኣቡኡ ኣነ እየ" ብምባል ባዕሉ ኣሚኑ ብምቕባል ቃሉ ዝሃበ እንተኾይኑ ኣቦ እቲ ቆልዓ ምዃኑ ተቐቢሉ ይበሃል፣
2. እቲ ዝሀቦ ቃል ዘስዕቦ ውፅኢት ፈሊጡ እዩ ዝተዛረቦ ኢልካ ምምርማር ኣድላይ ኣይኮነን፡፡

ዓንቀፅ 163. (3) ስርዓት (ፎርም)

ሓደ ሰብ ኣብ ቅድሚ ሓዳር መዝጋቢ ኣካል ብምቕራብ ኣቦ ምዃኑ ብምግላፅ ዝሀቦ ቃል ወይ ብፅሑፍ ብዝገብሮ ኑዛዘ ወይ ብኻሊእ ብዝኾነ ዓይነት ስልጣን ብዝተውሃቦ በዓል ስልጣን ብዝተረጋገፀ ሰነድ ኣቢሉ ኣቡኡ ምዃኑ ብምግላፅ ውላዱ ምዃኑ ምቕባል ይከኣል፡፡

ዓንቀፅ 164. ብዛዕባ ወኪልነት

1. ዋላ'ኳ ንኣካለ መጠን ዘይበፅሐ እንተኾነ ውላዳይ እዩ ኢሉ ቃል ክሀብ ዝኽእል ኣቦ ጥራሕ እዩ፣
2. ቃሉ ካሊእ ሰብ ክሀበሉ ምግባር ዝኽእል ብማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ዝፀደቐ ፍሉይ ስልጣን ውክልና ብምሃብ ጥራሕ ይኸውን፣
3. ብፍርዲ ዝተኸልከለ ሰብ ቃሉ ብባዕሉ ወይ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ እንትፈቅድ ብሽሙ ብሕጋዊ ወኪሉ ኣቢሉ ክሀብ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 165. ብዛዕባ ምምሟት ኣቦ

ኣቦ እቲ ቆልዓ ዝሞተ ወይ ፍቓዱ ክሀብ ዘይኽእል ኣብዝኾነሉ እዋን ካብ ንኣቡኡ ወላዲ ሓደ ክንድኡ ኮይኑ ነቲ ቆልዓ ክቕበሎ ይኽእል፡፡

ዓንቀፅ 166. ብዛዕባ ምቕባል ኣቦነት ኣደ ዘይምስማዕ

1. ኣደ እቲ ቆልዓ ነቲ ብኣቦነት ዝተቐበለ ሓቅነት ዘለዎ ምዃኑ እንድሕር ዘይኣሚና ኣቦ ውላደይ እዩ ኢሉ ዝሀቦ ቃል ኣብ ቅድሚ ሕጊ ውፅኢት የብሉን፣
2. ኣደ እቲ ቆልዓ ዝሞተት ወይ ፍቓዳ ክትገልፅ ዘይትኽእል ኮይና እንትትርከብ ነቲ ምእማን ቃል ካብ ወላዲ ኣደ ብሓዲኡ ክውሃብ ይኽእል፣

አንቀጽ 162. (2) ትርጓሜ

1. አንድ ሰው አንድን የተጸነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን የሚታወቀው "አባቱ እኔ ነኝ" ብሎ አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል፣
2. ይህ የሰጠው ቃል የሚያስከትለው ውጤት አውቆነው የተናገረው ብሎ መመርመር አስፈላጊ አይደለም፡፡

አንቀጽ 163. (3) ስርዓት (ፎርም)

አንድ ሰው , በጋብቻ መዝጋቢ ሰራተኛ ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሑፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ስልጣን በተሰጠው ባለስልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል፡፡

አንቀጽ 164. ስለወኪልነት

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው፣
2. ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚቻለው በማሕበራዊ ፍርድ ቤት የጸደቀ ልዩ የውክልና ስልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል፣
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 165. የአባትየው ስለመሞት

የልጁ አባት የሞተ ወይም ፍቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል፡፡

አንቀጽ 166. እናት የተቀባዩን አባትነት ስላለማመንዋ

1. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካለመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በህግ ፊት ውጤት አይኖረውም፣
2. የልጅ እናት የሞተች ወይም ፍቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ፣ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል፣

www.abyssinialaw.com



2. ውላዳይ እዩ ኢሉ ካብ ዝተቐበለ ሰብ ክጥንስ ዘይኽእል ምዃኑ ብዘየጠራጥር ኩነታት እንድሕር ዘይተረጋገፀ ተግባር ውላድ ምቕባል "ብስሕተት ወይ ብምትላል ዝተገበረ እዩ" ብምባል ምፍራስ ኣይከኣልን፡፡

ዓንቀፅ 172. ሓደ ቆልዓ ብዙሓት ኣቦታት ክቕበልዎ ብዛዕባ ዘይምኽኣሎም

ቅድም ክብል ብዛዕባ ውላድ ምቕባል ዝተውሃበ ቃል ክፈርስ እንድሕር ዘይተኼሩ ካሊእ ሰብ ውላደይ'ዩ ክብል ዝህቦ ቃል ተቐባልነት ኣይህልዎን፡፡

ንኡስ ክፍሊ ሳልሳይ
ብውሳነ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ኣቦነት ከፍለጥ ብዛዕባ ምግባር

ዓንቀፅ 173. (1) ብፍርዲ ብዛዕባ ዝንገር ኣቦነት

ብመሰረት ኣብ ላዕሊ ብዝተመልከቱ ድንጋጋት ኣቦ እቲ ቆልዓ ዘይተፈለጠ ወይ ዝተኸሓደ እንተኾይኑን ካብዚ ንታሕቲ ዝተመልከቱ ኩነታት እንትማልኡ ኣቦነት ብፍርዲ ውሳነ ክፍለጥ ይኽእል፣

ሀ. እቲ ቆልዓ ኣብ ዝተጠነሰሉ እዋን ኣብ ርእሲ ኣደ ምዕማፅ ወይ ምዝራፍ ተግባር ዝተፈፀማ እንተኾይኑ፣

ለ. ኮነ ተባሂሉ ዝተፈፀመ ተንኮል ተግባር ፤ ስልጣን ብዘይግቡእ ብምጥቃም ሓዳር ክገብረልኪ እየ ብምባል ተስፋ ቃል ብምሃብ ወይ ብኻሊእ ተመሳሳሊ መንገዲ እቲ ቆልዓ ኣብ ዝተጠነሰትሉ እዋን ኣብ ርእሲ ኣደ ናይ ምስሓት ተግባር ዝተፈፀማ እንተኾይኑ፣

ሐ. ኣቦ እዩ ብዝተብሃለ ሰብ ዝተፀሓፉን ኣቦነቱ ብዘየጠራጥር ዘረጋግፁን ደብዳቤታት ወይ ካልኦት ፅሑፋት እንትህልዉ፣

መ. ብሕጊ ዝተፈለጠ ርክብ እንክይሃለዎም ኣደን ኣቦ እቲ ቆልዓ እዩ ዝተብሃለ ሰብን ብሕጊ ኣብ ዝተመልከተ እዋን ጥንሲ ቀፃልነት ብዘለዎ ኩነታት ብርክብ ግብረ ስጋ ሓቢሮም ዝነበሩ እንተኾይኖም፣

2. ልጅ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊጸነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር፡ ልጅነትን የመቀበሉ ድርጊት "በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው" በማለት ሊፈርስ አይችልም፡፡

አንቀጽ 172. አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ በስተቀር ሌላ ሰው ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ንዑስ ክፍል ሦስት
